# ወንጌል ለሙስሊሞች

(የመምህሩ መምሪያ)

በጌርሃርድ ኔልስ

## ማውጫ

ገጽ


ሀ. መግቢያ . . . . . . . . . . . . . . . . 1
ለ. መሠረታዊ ሐሳቦች . . . . . . . . . . . . . 5
1. የእግዚአብሔር ቃል . . . . . . . . . . . . . 5
2. የእውነት ጥያቄ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 6
3. መነሻ ወይም መሠረተ ሀሳቦች . . . . . . . . . . 6
4. መረጃ ያለው እውነት . . . . . . . . . . . . 7
ሐ. የእስልምና እምነት መሠረቶችና መጽሐፍ ቅዱሳዊ ክርስትና ሲነጻጸሩ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 10
1. ኢየሱስ በእስልምና . . . . . . . . . . . 10
2. አላህ በእስልምና . . . . . . . . . . . 11
2.1. የቁርዓኑ አላህ ማነው? . . . . . . . . . . . . . 13
2.2. ሁባል ማነው? . . . . . . . . . . . . . . 14
2.3. ከዚህ የምንገነዘበውና የምንማረው ምንድነው? . . . . . . 19
3. እግዚአብሔርና አላህ . . . . . . . . . . . . . . . 20
4. የሰው ተፈጥሮ በቁርዓንና በመጽሐፍ ቅዱስ አመለካከት . . . . 32
4.1. መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ሰው ድርሻና ቦታ ያለው አመለካከት . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 32
4.2. ቁርዓን ስለ ሰው ድርሻና ቦታ ያለው አመለካከት . . . . 35
5. ቁርዓንና መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ኃጢአት ያላቸው አመለካከት . . 38
5.1 እስልምና ስለ ኃጢአት ያለው አገላለጽ . . . . . . . 43
5.2. ንስሐ፣ ይቅርታ፣ የኃጢአት ስርየት . . . . . . . . 49
5.3. ማጠቃለያ . . . . . . . . . . . . . . 50
መ. ወንጌልን ለሙስሊሞች የማድረስ መመሪያዎች . . . . . 52
1. የወንጌል ስርጭትን መገንዘብ . . . . . . . . . . . . 54
1.1. የወንጌል ስርጭት . . . . . . . . . . . . . 54
1.2. ወንጌል . . . . . . . . . . . . . . . . . 54
1.3. የወንጌል ሥራ መመሪያዎች . . . . . . . . . . 55
1.4. ደኅንነት በእስልምና . . . . . . . . . . . . 57
1.5. ለሙስሊሞች ወንጌልን ለማድረስ ቁርዓንን መጠቀም . . 59
1.6. የዐረቢኛ አባባሎችን የአጠቃቀም ዘዴ . . . . . . . . 60
1.7. ክርክርና የኑሮ ዘይቤ . . . . . . . . . . . . . 61
1.8. ወንጌልን ከአካባቢው ጋር የማስማማት ሂደት . . . . . 62
1.9. ከአካባቢው ጋር ስለማቀናጀር - ሙስሊማዊው አመለካከት . . . . . . . . . . 63
1.10. ፊት ለፊት መጋፈጥ አስፈላጊ ነው . . . . . . . . 64
1.11. ጥያቄ ስለ እውነት . . . . . . . . . . . . . 65
1.12. ያለ መግባባትን የማስወገጃ ዘዴ . . . . . . . . 66
2. ሙስሊሞችን መረዳት . . . . . . . . . . . . . 67
2.1. ‹በፍጽማን› መካከል ያለው ዝግብ . . . . . . . . 67
2.2. ‹አይነኪዎች› . . . . . . . . . . . . . . 76
2.3. የኃይል መመሪያ . . . . . . . . . . . . . 78
2.4. የሙስሊሞች ግፊት . . . . . . . . . . . . . 79
2.5. እስልምና በሁሉም ቦታ ገዢ እንዲሆን! . . . . . . . 81
2.6. ሙስሊሞች ‹በሕግ ሥር› ናቸው . . . . . . . . . 83
3. ባህልንና አስተዋፅኦውን መረዳት . . . . . . . . . . 85
3.1. የባህል ትርጉም . . . . . . . . . . . . . 85
3.2. ባህል ነክ የግንኙነት ችግሮች . . . . . . . . . 86
3.3. የነባራዊው ዓለም አመለካከት . . . . . . . . . 88
3.4. በትክክል መናገር . . . . . . . . . . . . . 89
3.5. እውነትን በፍቅር መናገር . . . . . . . . . . 89
4. ግንኙነትና ተግባሩን መረዳት . . . . . . . . . . . 90
4.1. ወንጌልን መስበክ ሊተላለፍ የማይቻለውን መልእክት ማስተላለፍ ነውን? . . . . . . . . . . 91
4.2. የግንኙነት ዘዴዎች . . . . . . . . . . . . 92

4.3. ተጨባጭና ሐሳባዊ ግንኙነት . . . . . . . . . . 97
1. የወንጌሉ እውነቶች . . . . . . . . . . . . 99
2. የወንጌሉ ማስረጃ . . . . . . . . . . . . . . 102
3. ወንጌሉ የሚጠይቃቸው ነገሮች ወይም ሁኔታዎች . . . 103
4. የወንጌሉ የተስፋ ቃሎች . . . . . . . . . . . 104
5. መንፈሣዊ ጦርነት . . . . . . . . . . . . . . . 106
5.1. ትንተና . . . . . . . . . . . . . . . . 107
5.2. ኃይል በወንጌል ስርጭት ውስጥ . . . . . . . . . 109
5.3. ‹የምንዋጋው› እንዴት ነው? . . . . . . . . . . 110
5.4. ምሳሌአችን . . . . . . . . . . . . . . . 113
5.5. አታላይና ‹የክልል› መናፍስት . . . . . . . . . 114
5.6. መንፈሳዊ ዕውርነትና እሥራት . . . . . . . . . 116
5.7. ከእስራት መፈታትና ነፃ መውጣት . . . . . . . . . 117
5.8. ማጠቃለያ . . . . . . . . . . . . . . . 117
5.9. በእስልምና ያለ የባላጋራነት ግጥሚያ . . . . . . . . 118
ሐ. ሙስሊሞችን በወንጌል የመድረስ ተግባራዊ ሁኔታዎች . 120
1. በቅድሚያ መጤን ያለባቸው ነገሮች . . . . . . . . . 120
2. ‹ጌታ ሆይ እኔ ማን ነኝ?› . . . . . . . . . . . . 121
3. ትክክለኛውን አመለካከት እንፈልግ . . . . . . . . . 122
1. የመስማማት (የመደራደር) አመለካከት . . . . . . . . 122
2. የመዝመት (የዘማች) አመለካከት . . . . . . . . . 123
3. ሚሲዮናዊ አመለካከት . . . . . . . . . . . . 123
4. ችሎታዎች . . . . . . . . . . . . . . . . . 125
5. ዝግጅትና ልምድ . . . . . . . . . . . . . . . 127
6. ተግባራዊና ባህላዊ ግምገማዎች . . . . . . . . . . 128
ረ. ለሙስሊም ወንጌል የማድረስ ዘዴ . . . . . . . . . . 139
1. ዓላማውና እቅዱ . . . . . . . . . . . . . . 139
2. ማጠቃለያ . . . . . . . . . . . . . . . . . 139

## ሀ. መግቢያ

**ይህ መጽሐፍ የመምህሩ መመሪያ እንጂ ያለአስተማሪ ለማጥናት ለሚፈልጉ የተዘጋጀ አይደለም።**

የመምህሩ መምሪያ መጽሐፍ እንደ ሌሎች መጻሕፍት ለማንበብ ቀላል አይደለም፤ ምክንያቱም የመጽሐፉን ይዘት በሙሉ በተገቢው መንገድ መረዳት ስለሚያስፈልግ ነው።

ይህ መጽሐፍ ወንጌልን ለሙስሊሞች ለማድረስ የሚዘጋጁትን አገልጋዮች ለሚያሠለጥነው ሰው ጥልቀት ያለውና መሠረታዊ ሐሳብ ይሰጣል። መምህሩም ከዚህ ተነሥቶ የበለጠ ጥናት በማድረግ የሚያስተምርባቸውን ዘዴዎች መምረጥ አለበት። የሚመርጣቸውም ዘዴዎች ተማሪዎቹ በሥራም ሆነ በሌላ መንገድ ሊገኙአቸው ከሚችሉት ሙስሊሞች ጋርና ከእስልምና እምነታቸው ዓይነት ጋር ተጓዳኝ መሆን አለበት። በዚህ ዓይነት መንገድ የተጻፉትን መጻሕፍት በስፋትና በጥልቀት ለማንበብ ብትፈልጉ «ወንጌልን ለሙስሊሞች ለማድረስ መነሻ ‘ሐሳቦችና መመሪያዎች» የተባለውን መጽሐፍ እንድንልክላችሁ ልትጽፉልን ትችላላችሁ።

በዚህ መጽሐፍ ውስጥ አንዳንድ የሐሳብ ድግግሞሽእንዳለ ብናውቅም ለማስወገድ ግን አልወደድንም። አንዳንዶቹ ሃሳቦች የሚደጋገሙት ትኩረት እንዲሰጥባቸው ስለተፈለገ ሲሆን፥ ሌሎቹ ደግሞ ከተለያዩ ርዕሶች ጋር ግንኙነት ስላላቸው ነው።

ማንኛውም በጥበብና በማስተዋል ለሙስሊሞች ወንጌልን መመስከር የሚፈልግ ሰው ስለ እስልምና አንዳንድ መሠረታዊ ዕውቀት እንዲኖረው ያስፈልጋል፤ («እስልምና ስለ ራሱ ያለው አመለካከት፥ ሌሎች ያላቸው አመለካከትና የእስልምና ምንነቱ» በሚለው ርዕስ ሥር የተጠቀሰውን ተመልከት።) በተጨማሪም እስልምና ስለ ክርስትና ያለውን አመለካከት መረዳት ያስፈልጋል። («የእስልምናና የክርስትና ግጭቶች» በሚለው ርዕስ ሥር የተጠቀሰውን ተመልከት።) ሌላ ባሻገር የሙስሊሞችን አመለካከት፥ በሃይማኖት መሐል ሊፈጠር የሚችለውን ግጭት፥ ባህላዊ ጉዳዮችን፥ የግንኙነት ዘዴዎችን፥ እንዲሁም አንዳንድ ተግባራዊ የሆኑ ወንጌልን የማስተላለፍ ዘዴዎችን መረዳት ያስፈልጋል። ይህ መጽሐፍ እነዚህ ከላይ የተጠቀሱትን ነገሮች ለማቅረብ የሚሞክር ነው። ነገር ግን ከዚህ በመነሣት ለሙስሊሞች ፈጣን መልስ ሰጥተን ቅፅበታዊ ውጤት መጠበቅ የለብንም። ይህን ብናደርግ ብዙ ጥፋት ልናደርስ እንችላለን። ይህ መጽሐፍ የሦስት ተከታታይ መጻሕፍት አንደኛው ክፍል መሆኑን ላስገነዝባችሁ እወዳለሁ። ሙሉ ግንዛቤ ለማግኘት መጻሐፍቱ በሙሉ መጠናት

አለባቸው።

## ወንጌልን ለሙስሊሞች ማድረስ ማለት «ምን ማለት ነው?» «እንዴትስ» ነው የሚፈጸመው?

ስለ እነዚህ ሁለት መሠረታዊ ጥያቄዎች ግንዛቤ ማግኘት አስፈላጊ ነው። «ምን ማለት ነው» የሚለው ጥያቄ መሠረታዊ ዕውቀትን ያመለክታል። የእስልምና ይዘት ምን እንደሆነ፥ አንድ ሙስሊም የራሱን እምነትና የክርስትናን እምነት እንዴት እንደሚረዳ ወዘተ ... የሚለውን ሁሉ ያጠቃልላል። ከእነዚህ አንዳንዶቹ በጣም ስሜትን ሊጎዱ የሚችሉ ስለሆኑ ያለ አግባብ ከተጠቀምንባቸው ተቃውሞንና ለየወንጌል ሥራ የተከፈተውን በር ሊዘጉ ይችላሉ። ሆኖም እስልምናንና ሙስሊሞችን ለመረዳት እነዚህን ማወቅ አለብን። ከሙስሊሞች ጋር በምናደርገው ግንኙነት፥ እነዚህ ስሜት የሚነኩ ጉዳዮችን ከእነርሱ ጋር የምንካፈልበት ጊዜ መምጣቱ አይቀርምና። «እንዴት» የሚለውንም ጉዳይ መመልከት አለብን። ማካፈል ያለብንን ነገር የምናካፍልበት መንገድ እጅግ በጣም ልናተኩርበት የሚገባ ጉዳይ ነው። ይህም እጅግ ብዙ ጥንቃቄ የሚያስፈልገው ስለሆነ፥ በፍጹም በቀላሉ መታየት የለበትም።

«ወንድሞች ሆይ በአዕምሮ ሕፃናት አትሁኑ፤ ለክፋት ነገር ሕፃናት ሁኑ እንጂ፤ በአዕምሮ የበሰሉ ሁኑ።» (1 ቆሮ 14:20)።

## ወንጌልን ለሙስሊሞች ማድረስ የተቀደሰ ጥሪ ነው

የጠራን ቅዱስ ስለሆነ፥ ወንጌልን የመስበክና ደቀመዝሙር የማድረጉ ጥሪ ሁሉ የተቀደሰ ነው። ጌታችን ኢየሱስ ራሱ እንዲህ ብሏል:-

> «ሥልጣን ሁሉ በሰማይና በምድር ተሰጠኝ፤ እንግዲህ ሂዱና አሕዛብን ሁሉ... ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸው ደቀመዛሙርት አድርጓቸው። እነሆ እኔ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ» (ማቴ 28:18-20)።

ሁላችንም የዚህን ቃል የመጨረሻ ክፍል ለራሳችን ለማድረግ እንፈልጋለን። ነገር ግን እኔ የመጀመሪያውና የመጨረሻው ክፍል የተያያዙ መሆናቸውን አያለሁ።

> ‹እኔ ከእናንተ ጋር ነኝና ሒዱ› ነው የሚለው። «... ጌታ ስለ ተስፋ ቃሉ አይዘገይም፤ ነገር ግን ሁሉ ወደ ንስሐ እንዲደርሱ እንጂ፥ ማንም እንዳይጠፋ ስለ እናንተ ይታገሣል» (2 ጴጥ 3:9)።
>
> «ሰዎች ሁሉ ሊድኑና እውነቱን ወደ ማወቅ ሊደርሱ በሚወድ በእግዚአብሔር በመድኀኒታችን ...» (1 ጢሞ 2:4)።



> «እንግዲህ ያላመኑበትን እንዴት አድርገው ይጠሩታል? ባልሰሙትስ እንዴት ያምናሉ? ያለ ሰባኪስ እንዴት ይሰማሉ?» (ሮሜ 10:14)።

ወንጌልን ከሰሙ በኋላ ለሰሙት ወንጌል አዎንታዊ ምላሽ በሰጡት በብዙ አገሮችና ሕዝቦች ብንደሰትም፥ የመስማት ዕድል ያላጋጠማቸው እንዳሉም ልናስብ ይገባል። ወንጌል ካልደረሳቸው የሕዝብ ክፍሎች አንዱና ከፍተኛው የሙስሊሙ ኅብረተሰብ ነው። በአሁኑ ወቅት ከዓለም ሕዝብ ከ1 ቢሊዮን በላይ የሚገመተው ሙስሊም እንደሆነ በራሳቸው በሙስሊሞች ይነገራል። ባጠቃላይ ስንመለከተው አባባሉ ተቀባይነት ያለው ነው፤ ነገር ግን ይህ ቁጥር የሥነ-ልቦና ተፅዕኖ ለማድረግ በጥንቃቄ ታስቦበት የሚነገር ነው።

## ለመሆኑ ከአፍሪቃ ሕዝብ ግማሹ ሙስሊም መሆኑን ታውቃለህን?

ለሰዎች ሁሉ ወንጌልን ለማድረስ ብታስብ ምን ያህል የወንጌል ሠራተኞችን ወደ ሙስሊሞች ትልካለህ? ከአሉኝ ግማሾቹን፥ ወይም ከግማሽ በላይ የሆኑትን ብለህ መለስክ? እኔም እንዲሁ ነው የማደርገው። ሆኖም ግን እንደ ኤሮፓውያን አቆጣጠር በ1975 ዓ.ም. በአፍሪቃ ከሚያገለግሉት 16000 ሚስዮናውያን መሐል 250 ብቻ ከአፍሪቃ ሕዝቦች ግማሽ ወደሆነው ወደ ሙስሊሙ ኅብረተሰብ ሄደዋል። የእግዚአብሔርን ታላቅ ተልእኮ ለመታዘዝ እኔ የምመክረው ነገር ቢኖር ከሙስሊሞች አቅራቢያ የሚኖር እያንዳንዱ የክርስቶስ ተከታይ ራሱን በማዘጋጀት ወደ ሙስሊም ጎረቤቶቹ፥ ወይም የሥራ ባልደረቦቹ ሄዶ መልካሙን የምሥራች ትርጉም ባለውና ሊገባቸው በሚችል መንገድ ማካፈል እንዳለበት ነው!

## ወንጌልን ለሙስሊሞች ማድረስ ለምን አስፈለገ?

ለሙስሊሞች ማድረስ ያስፈልጋል፤ ምክንያቱም:-

1. ያለ ጥርጥር የእግዚአብሔር ፈቃድ ነው።
2. እኛ ለእግዚአብሔር ያለን ፍቅር የሚለካው እሱ ላዘዘን ነገር በመታዘዛችን ነው።
3. የሙስሊሙ ኅብረተሰብ እ.ኤ.አ. በ1900 ዓ.ም. 150 ሚሊዮን ነበር። በአሁኑ ወቅት ግን 1100 ሚሊዮን ደርሷል፤ (ይህ ዕድገት በአብዛኛው በጋብቻ ምክንያት እንደሆነ ይታመናል)።
4. የሙስሊሞች የኤኮኖሚ ዕድገት ከፍተኛ በመሆኑ፥ (ከነዳጅ ሀብት የሚገኘው ወሰን የሌለው ገንዘብ ለከፍተኛ ትምህርትና እስልምናን ለማስፋፋት ይውላል)።

5. የሙስሊሞች ፖለቲካዊና ርዕዮተ-ዓለማዊ ዕድገት በመኖሩ፥ (ከቅኝ አገዛዝ ነፃነት በኋላ)።

6. በእስልምናው አካባቢ ቤተ ክርስቲያንን የሚገዳደር የሚሲዮናዊነት ሥራና እንቅስቃሴ በሁሉ ቦታ በመጀመሩ ነው።

7. እስልምና ራሱን የሚገልጽበት መንገድ እንደሚከተለው ዓይነት የተሳሳተ በመሆኑ

ሱረቱ 3፡110፡- ለሰዎች ከተገለጹት ሕዝብ ሁሉ
በላጭ ሆናችሁ፤ በጽድቅ ነገር
ታዛላችሁ፤ ከመጥፎም ነገር
ትከለከላላችሁ በአላህም
(አንድነት) ታምናላችሁ።

118፡- እናንተ ያመናችሁ ሆይ!
ከእናንተ ሌላ ምስጢረኛ
አትያዙ፤ ማ በላሸትን
አይገቱላችሁም፤ ጉዳታችሁን
ይወዳሉ፤ ጥላቻይቱ
ከአፎታቸው በእርግጥ
ተገለጸች፤ ልቦቻቸውም
የሚደብቁት ይበልጥ ትልቅ ነው።

ከዚህ የተነሣ እንኳ እስልምና ራሱን እንደሚገልጸው፥ በወግ አጥባቂነት፥ በግብታዊነትና በአክራሪነት ታላቅ ቀውስ ውስጥ ቢሆንም፥ ሙስሊሞች ቁርዓን እንደሚያስተምራቸው በራሳቸው ይደሰታሉ። እስልምና «ዘመናዊነትን» ማለትም ጥልቀት ያለው የቁርዓንና የሐዲስ ጥናት ሊያመጣ የሚችለውን መዘዝ፥ ትምህርትና ሥነምግባርን ከሃይማኖት ለይቶ የማየቱን ጉዳይና ግለኛነትን ይፈራል። ለነዚህ ነገሮች የእስልምና ምላሽ፡- ሕጎችና ደንቦች፥ እገዳዎች የሙስሊሞችን አዕምሮ እንደወተት መጋትና እንደ ሰዓት መሙላት እንዲሁም በሐዲስ ላይ የሚቀርቡትን ሐሶች ሙሉ በሙሉ አለመቀበል ናቸው።

ይህ ነገር አብዛኛው ሙስሊሙ ጥልቅ የሆነ መንፈሳዊ ባዶነት ተሰምቶት እኛ ልንመልሰው የሚገባንን ጥያቄ ይጠይቃል፡ (1 ጴጥ. 3፡15)

በመጨረሻ ስናጠቃልል፡-

1. እስልምና የሚያስተምረው «ልዩ ወንጌል» (ገላ 1፡6-9) እና «ሌላ ኢየሱስ»ን (2ኛ ቆሮ 11፡2-4) ነው።



2. የእግዚአብሔር ፈቃድ፡- ሁሉ ወደ ንስሐ እንዲደርሱ (2 ጴጥ 3፡9)

- ማንም እንዳይጠፋ (2ኛ ጴጥ. 3፡9)
- ሁሉ እንዲድን (2ኛ ጢሞ.2፡4)
- ሁሉ እውነትን ወደማወቅ እንዲደርሱ (1 ጢሞ. 2፡4) ነው።

3. ስለዚህም እግዚአብሔር ደቀመዛሙርቱን ወደ ዓለም ሁሉ እንዲሄዱ አዟል፤ (ማቴ. 28፡18-20፤ ማር. 16፡15-18) ጌታ ደቀመዛሙርቱን (በዛሬው ዘመን እኛን ማለት ነው)

«እስኪመጣ ድረስ በሰጣቸው መክሊት እንዲነግዱ» አዟል። (ሉቃ 19፡13)

## ሀ. መሠረታዊ ሐሳቦች

ሁሉም ክርስቲያን ለጌታችን ኢየሱስና ለክርስትና እምነት ምስክር እንዲሆን ተጠርቷል።

«ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በወረደ ጊዜ ኃይልን ትቀበላላችሁ ...እስከ ምድር ዳርም ድረስ ምስክሮቼ ትሆናላችሁ፤» (የሐዋ. 1፡8)

ሁላችንም ወንጌላውያን ባንሆንም፥ ሁላችንም ምስክሮቹ እንድንሆን ተጠርተናል!

ሙሉው ወንጌል
በሙሉዋ ቤተ ክርስቲያን
ለመላው ዓለም።
መላው ዓለም ሙስሊሞችንም ሁሉ ይጨምራል!

በአብዛኛው ሙስሊሞች ባሉበት እንዲሁም በእስልምና ሕግ በሚተዳደሩ አገሮች ውስጥ ያሉትንና በክርስቲያኖች መሐልና አቅራቢያ ለሚኖሩ ሙስሊሞች ወንጌልን የምናደርስበት ዘዴ የተለያየ መሆን እንዳለበት ግልጽ ነው። የዚህ ጥናት ዓላማ በሙስሊሞች አካባቢ የሚኖሩትንና ከሙስሊሞች ግላዊና ማኅበራዊ ግንኙነት መፍጠር የሚችሉትን ክርስቲያኖች ለማዘጋጀት ነው።

## 1. የእግዚአብሔር ቃል

እንደ ሌሎች መጻሕፍት ሁሉ ልንረዳው ይገባል። ከዚያ በኋላ ልናምነው ይገባል።

«እኛ ግን ከእግዚአብሔር እንዲያው የተሰጠንን እናውቅ ዘንድ ከእግዚአብሔር የሆነውን መንፈስ እንጂ የዓለምን መንፈስ አልተቀበልንም። መንፈሳዊውን ነገር

ከመንፈሳዊ ነገር ጋር አስተያይተን መንፈስ በሚያስተምረን ቃል ይህን ደግሞ እንናገራለን እንጂ የሰው ጥበብ በሚያስተምረን ቃል አይደለም።» (1 ቆሮ. 2፡12-13)

« ... የክርስቶስን ምሥጢር እንድንነግር እግዚአብሔር የቃሉን ደጅ ይከፍትልን ዘንድ ስለ እኛ ደግሞ ጸልዩ፤ ልናገር እንደሚገባኝ ያሀል እገልጠው ዘንድ ጸልዩልኝ።» (ቆላ 4፡3-4)

በዚህ መጽሐፍ ለሙስሊሞች ወንጌልን ማድረስ «እንዴት» ይፈጸማል? በሚለው ጉዳይ «መልካሙን ዜና ለማስተላለፍ በጣም ውጤታማ የሆነውን መንገድ እናያለን። «እነሱ ያውቁ ዘንድ» «መንፈሳዊ ነገር ጋር አስተያይተን» «ልንናገር የሚገባንን ያሀል እንገልጣለን»።

እስልምናና መጽሐፍ ቅዱሳዊው የክርስትና እምነት ከሚመሳሰሉበት ነገር ባሻገር፥ በፍጹም ሊገናኙ የማይችሉ ነገሮች እንደሆኑ አይተናል። ሊታረቁ በፍጹም አይችሉም። ሁሉም ሙስሊም ይህን ነገር በልቡ ያውቃል። በመሆኑም «ይሀ-ወይስ ...» የሚለውን ማማረጫ አስከትሏል።

## 2.የእውነት ጥያቄ

ሙስሊሙም ክርስቲያኑም የየራሳቸውን እምነት አጥብቀው ይዘው፥ በዓይነ ቁራኛ እርስ በርስ የሚጠባበቁ ናቸው። ፋይዳቢስና ትርጉም የለሽ ክርክሮችንና ግጭቶችን ለማስወገድ ሁለት ነገሮችን መጠቀም አለብን።

**ሙስሊሙንና እስልምናን መረዳት እና ትክክለኛና እውነተኛ ግንኙነት ማድረግ**

ይህንን መወጣት መቻል የዚህ የሦስተኛው ጥናታችን ርዕሰ-ጉዳይ ነው።

## 3. መነሻ ወይም መሠረተ ሐሳቦች

የሚከተሉት ጥያቄዎች በቅንነትና በታማኝነት ሊመለሱ የሚገቡ ናቸው፥

1. መሐመድን፡- ሰውን ሁሉ በአንድነት የሚጠቀልል፥ ቁርዓንና ትርጓሜውን (ጣፍሲር በሱና አማካኝነት) ለርሱ የተሰጠው፥ የመጨረሻና ዓለም አቀፋዊ የእግዚአብሔር መልእክተኛ (ነቢይ) እንደሆነ አድርገን ለመቀበል እንችላለን?



2. ቁርዓን ከአዲስና ከብሉይ ኪዳን (ቁርዓን መልዕክቱ ተዛብቷል ከሚላቸው መጻሕፍት) ቀጥሎ የመጣ ሙሉና የመጨረሻ የእግዚአብሔር መገለጥ ለመሆኑ እንስማማለን?
3. ነቢ ዒሣ («ነቢዩ ኢየሱስ») በቁርዓንና በእስልምና ውስጥ በቀረበበት ሁኔታ እንስማማለንን?
4. ማንነቱ በቁርዓንና በሐዲስ የገለፀው አላህ፥ በመሠረታዊ ባሕሪው፥ የአብርሃም፥ የይስሐቅ፥ የያዕቆብ ወይም የእስራኤል አምላክ የሆነው፥ እግዚአብሔር እርሱ ራሱ ደግሞ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አባት ነውን?
5. በመጽሐፍ ቅዱስና በቁርዓን ስለ ሰው፥ ስለ ኃጢአት፥ ስለኃጢአት ይቅርታ የተገለጸው ሐሳብ አንድ ዓይነት ወይም ተመሳሳይ ነውን?

ለነዚህ ጥያቄዎች ትክክለኛ መልስ መስጠት የእኛንና የሙስሊሞችን አቋም ይወስናል። አስተውለን መፍረድ የምንችል ከሆነ፥ የአምስቱም ጥያቄዎች መልስ «አይደለም» መሆኑ ግልጽ ነው።

መጻሕፍትን፥ እምነቶችን፥ ሃይማኖቶችንና ትምህርቶቻቸውን ተጨባጭ በሆነ መንገድ ለማጥናትና ለመመርመር የሚጠይቀው ነገር፡-

## 4. መረጃ ያለው እውነት

በክፍል 1 «እስልምና - ስለ ራሱ ያለው አመለካከት፥ ሌሎች ያላቸው አመለካከት፥ ምንነቱ» በሚለው ርዕስ ሥር ገጽ 26-45፥ 51-78፥ 80-89፥ 92 ሀ-ሐ ያለውንና
በክፍል 2 «የእስልምናና የክርስትና ግጭቶች» በሚለው ርዕስ ሥር ገጽ 36-49 ና 50-82 ተመልከት።

በዚህ ክፍል የመጽሐፍ ቅዱስና የቁርዓን የተለያዩ ትምህርቶች በግልጽ ተቀምጠዋል። እንዲሁም መጽሐፍ ቅዱስ ያለው የማስረጃ ድጋፍና በቁርዓን በኩል የማስረጃ መታጣት በግልጽ ተቀምጧል። ይህ ደግሞ እስልምና ሊያቀርበው በሚሞክረው «ማስረጃ» ጭምርም ሊካድ የማይቻል ነው።

ከመጽሐፍ ቅዱስ ሌላ፥ ከመለኮታዊ ምንጭ እንደመጣ ተጨባጭ ማስረጃ ያለው አንድም የሃይማኖት መጽሐፍ እንደሌለ በእርግጠኝነት መናገር እንችላለን።

ይህ ደግሞ ሕይወታችንን በቃሉ ላይ ለመመሥረት በቂ ምክንያት ነው። በተጨማሪም መጽሐፍ ቅዱስ የሌሎች «መገለጦች» ሁሉ መለኪያ ነው።


«መለካት» ማለት ከመመዘኛው ጋር ማወዳደር ማለት ነው። ለክርስቲያኖች መለኪያ የእግዚአብሔር ቃል የሆነው፥ መጽሐፍ ቅዱስ ነው። ለሙስሊሞች ደግሞ ቁርዓን ነው። ክርስቲያኖቹም ሆነ ሙስሊሞቹ ውድ የሆኑትን መጽሐፎቻቸውን ከልባቸው ያምናሉ ይከተላሉም። ይህ ግን ብዙ ጊዜ አእምሮን የሚጨምር አይደለም። ተጨባጭ የሆኑ እውነታዎችን ስንመለከት ደግሞ አእምሮአችንንም መጠቀም አለበን!

ክርስቲያኖችና ሙስሊሞች ምን እንደሚያምኑ ማወቅ አለባቸው። ይህን ቢያንስ በተወሰነ ደረጃ ብዙዎች ያውቃሉ። ቢሆንም ቅሉ አብዛኛዎቹ ክርስቲያኖችና ሙስሊሞች «ለምንድን ነው ይህን የምታምነው?» የሚለው ጥያቄ ሲቀርብላቸው፥ ብዙ ጊዜ በጣም ሐሳባዊና ተጨባጭነት የሌለው መልስ ነው የሚሰጡት።

እግዚአብሔር ‹ልብንም› አእምሮንም ሰጥቶናል። በእምነት ጉዳዮቻችን ላይ እነዚህ ነገሮች መጠቀም አለብን በተቃራኒው፥ ማስተዋል ባለበት፥ እውነት በሆነው፥ በሐቀኛ ምክንያታዊነትና ሐሳብ ላይ አእምሮአችንን ብናጨልም የመታለል ዕድላችን በጣም ሰፊ ይሆናል።



ስለዚህ ነገር አደገኛነት አውቀን መጠንቀቅ ብቻ ሳይሆን፥ ሙስሊሞችንም በዚህ ጉዳይ ላይ ልናስጠነቅቃቸው ያስፈልጋል። እኔ የሚከተለውን ምሳሌ በመጠቀም ብዙ ጊዜ ይህን አድርጊያለሁ፥



## ሐ. የእስልምና እምነት መሠረቶችና መጽሐፍ ቅዱሳዊ ክርስትና ሲነፃፀሩ

ኢየሱስ ክርስቶስ «እኔ መንገድና እውነት ሕይወትም ነኝ። በእኔ በቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም፤» ብሏል። (ዮሐ. 14:6)።

«መዳንም በሌላ በማንም የለም፤ እንድንበት ዘንድ የሚገባን፥ ለሰዎች የተሰጠ ስም ከሰማይ በታች ሌላ የለምና።» (ሐዋ 4:12)።

እነዚህን ሁለት ዕስረፍተ ነገሮች ሰዎች ሊቀበሏቸው የማይፈልጉትን ያህል ግልጽ ናቸው። እንደ ክርስቲያን እኛ እናምናቸዋለን። የምናምናቸውም በበቂ ምክንያት ነው። («የወንጌል መረጃዎች» በሚለው ሥር የተጠቀሰውን ተመልከት)!

### ኢየሱስ በእስልምና

ሙስሊሞች የሚያምኑት:-

1. ኢየሱስ መለኮታዊ፥ ወይም የእግዚአብሔር ልጅ እንዳልሆነና አንድ ወደ አይሁዳውያን ዘንድ የተላከ የእግዚአብሔር መልእክተኛ እንደሆነ ነው።
2. ኢየሱስ ተፈጥሮአዊ የሆነውንም ሞት ሆነ፥ ስለ ኃጢአተኞች ብሎ በመስቀል ላይ አልሞተም። ስለዚህ ሊያድን አይችልም፤ አያድንምም።
3. እስልምና ጠቅላላውን የሥርየትና የዕርቅ ትምህርት የሚቃረነው፥ ኢየሱስ ለእኛ በሞተልን ጊዜ የኃጢአታችንን ዋጋ ለመክፈል ያቀረበውን የላቀ መሥዋዕት የሚቃረነውን ያህል ነው።
4. መጽሐፍ ቅዱስ በነዚህና በሌሎችም ጉዳዮች ላይ ቁርዓንን ስለሚቃረን፥ ሙስሊሞች የራሳቸውን አቋም እውነተኛነት ለማረጋገጥ ይፈልጋሉ። ይህንንም የሚያደርጉት መጽሐፍ ቅዱስ በቁርዓን የተሻረ (የተተካ) መሆኑን በማወጅ ነው፤ (ከዚሁ መጽሐፍ ገጽ 1-15)።
5. የመጨረሻውና ዓለም አቀፋዊው የአላህ መልእክተኛ ቁርዓን የተገለጠለት መሐምድ ነው። ምንም እንኳ መሐመድ ማስጠንቀቂያ ሰጪ ከመሆኑ ሌላ ምንም እንዳልሆነ ቢነገርም እውነቱን ስንመለከት ለክርስቶስ የሚገባው ክብር ሲሰጠው እናያለን። ሳሙኤል ዘዌመር የተባሉት ሰው «የሙስሊሞች ክርስቶስ» በተባለው መጽሐፋቸው «በሁሉም ተግባራዊ ዓላማዎች ስናየው፥ መሐመድ ራሱ የሙስሊሞች ክርስቶስ ነው» ብለዋል። እንዲሁም እኚሁ ሰው «መሐመድ በሞቱና በሕይወቱ ክርስቶስን እንዲመስል ተደርጎ ቀርቧል» ብለዋል። ሆኖም ግን በቁርዓን ስለ ኢየሱስና ስለመሐመድ የተገለጸውን



ብናወዳድር የተባለውን ለመቀበል በጣም ያስቸግራል።
ቁርዓን ስለ ኢየሱስ የሚከተለውን ያስተምራል:-

* ከድንግል እንደተወለደ (ሱረቱ 19:16-35)
* መሢሕ እንደሆነ (ሱረቱ 4:171)
* የእውነት ቃል እንደሆነ (ሱረቱ 19:34)
* ቅዱስ እንደሆነ (ሱረቱ 19:19)
* በአሁኑና በሚመጣው ዓለም የተከበረ እንደሆነ (ሱረቱ 3:45)
* ለሰው ሁሉ ምልክት መሆኑን (ሱረቱ 21:91፤ 19:21)
* የሕይወት ፈጣሪ መሆኑን (ሱረቱ 3:49፤ 5:113፤ (22:73) ተመልከት
* ከእግዚአብሔር የተሰጠ ምሕረት መሆኑን (ሱረቱ 19:21)
* ከእግዚአብሔር የወጣ መንፈስ መሆኑን (ሱረቱ 4:171)
* የእግዚአብሔር ቃል መሆኑን (ሱረቱ 4:171)። የእግዚአብሔር ቃል፥ (የእግዚአብሔር አሳብ፥ አእምሮ) ክፍል ነው ወይስ የተለየ አካል ነው?
* ወደ ሰማይ ያረገ መሆኑን (ሱረቱ 4:158)
* ለመፍረድ እንደሚመለስ (ሱረቱ 13:61 ከሚሽካት 4 ገጽ 78-80)
* ተአምር ሠሪ መሆኑን (ሱረቱ 3:49) ያስተምራል።

### አላህ በእስልምና

ለእስልምናና ለመጽሐፍ ቅዱስ ተማሪዎች ግልጽ እንደሆነው አላህ፥ ከአብርሃም ከይስሐቅና ከያዕቆብ አምላክ ከእግዚአብሔር ጋር አንድ እንዲሆን ተደርጎ ተወስዷል፤ ይህ ትምህርትም ይሰጣል። መሐመድም እንዲሁ ነው ያስተማረው። ቁርዓንም ይህን ግልጽ አድርጎታል።

ሱረቱ 29:46 የመጽሐፉን ባለቤቶችም

በዚያች እርሷ መልካም በሆነችው
ክርክር እንጂ አትከራከሩ።
ከነሱ እነዚያን የበደሉትን
ይቀር በሉም:- በዚያ ወደ እኛ
በተወረደው፥ ወደ እናንተም በተወረደው፥
አመንን፤ አምላካችንም አምላካችሁም
አንድ ነው፤ እኛም በእርሱ ታዛዦች ነን።

ሱረቱ 2፡ 136 በአላህና ወደኛ በተወረደው (ቁርዓን)
ወደ ኢብራሂምም ወደ ኢስማኤልና
ወደ ኢስሐቅም በተወረደው፥
በዚያም ሙሳና ዒሣ በተሰጡት፥
በዚያም ነቢያት ሁሉ ከጌታቸው
በተሰጡት፤ ከእነርሱ በአንድም መካከል
የማንለይ ስንሆን አመንን፤
እኛም ለእርሱ (በአላህ) ታዛዦች ነን በሉ።

(ሱረቱ 3፡2-3፤ 4፡136፤ 5፡47፥ 71፤ 10፡17፥ 94፤ 6፡92፤ 4፡47፤ 21፡7 አንብብ)።

ሙስሊሞች የሚያምኑት ይህንን ነው ተብሎ ይገመታል። ስለ እግዚአብሔር ያላቸው ዕውቀት ደግሞ ከአጋርና ከእስማኤል (ከ2000 ዓ.ዓለም-610 ዓ.ምህረት) ጀምሮ ባለው ጊዜ በአፍ በተላለፈላቸው መልእክት በኩል ያገኙት መሆኑን ያምናሉ። ይህ የአላህ አምልኮ፥ መሐመድ ከመምጣቱ በፊት በነበሩት ጣዖት አምላኪ ዐረቦች ለጊዜው ታግዶ ቢቆይም፥ በአብርሃም አምላክ በሚያምኑ ሐኒፎች አማካኝነት እንደገና ተጀመረ፤ («እስልምና ስለ ራሱ አመለካከት፥ ሌሎች ያላቸው አመለካከትና ምንነቱ» ገጽ 160ን ተመልከት)። (ይህ እውቀት በዐረቢያ ከሚኖሩ አይሁዶችና ክርስቲያኖች ነው ወደ ዐረቦች የመጣ ነው)። ከዚህ በኋላ መሐመድ መልአኩ ገብርኤል ተገልጦለት የመጨረሻ የአላህ መገለጥ የሆነውን ቁርዓንን በ23 ዓመታት ውስጥ ተቀበለ። አሁን ቁርዓን በሰዎች የተዛቡትንም ሆነ የጠፉትን የበፊቶቹን መገለጦች ሁሉ እየተካ ነው። መጽሐፍ ቅዱስን ጨምሮ ‹ሁሉም የበፊቶቹ መገለጦች› በመጀመሪያ በሰማይ ካልተጻፈውና ዘላለም ከሚኖረው ከቁርዓን ጋር አንድ ዓይነት ነበሩ። ለዚህም እውነተኛው ቅጂ የዐረብኛው ቁርዓን ብቻ ነው። የአላህ እውነተኛ ሀሳብ በቁርዓን ውስጥ ብቻ ይገኛል።

እዚህ ላይ ችግሮች ይፈጠራሉ፡-

1. አላህ ከመሐመድ በፊት ለብዙ ዘመናት እንደ ባዕድ አምላክ የሚታወቅና በአረማውያን ዘንድ የሚመለክ ነበር እንጂ፥ ሰዎች ሳይረዱት በተዛባ መልኩ የሚያመልኩት የአብርሃም አምላክ በፍጹም አልነበረም። በመሐመድ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መልክ የተሰጠውንና ነገር ግን በባሕርይውና በውስጠ-ምስጢሩ ልዩ የሆነውን እንዲህ ያለ አምላክ እንዴት ልንቀበል እንችላለን?
2. የእግዚአብሔርን ኤሎሒምን (በመጽሐፍ ቅዱስ) እና የአላህን (በቁርዓን) ገለጻ ስንመለከት በዝርዝርና ጥቃቅን ጉዳዮች ላይ በፍጹም የማይገናኙ ናቸው።



ቢሆንም ቅሉ ሁለቱም ፈጣሪነታቸው፥ ሁሉን ቻይነታቸው ወዘተ... እና በመጨረሻው ቀን በሰው ልጆች ላይ እንደሚፈርዱ ተገልጿል።

3. የእስልምና ብቸኛ ምስክር የሆነው መሐመድ በመጽሐፍ ቅዱስ መመዘኛዎች ነቢይ ሊሆን አይችልም፤ ምክንያቱም የመሐመድ መልእክት በ1400 ዓመታት ውስጥ ቃሉ እየተገለጸላቸው መጽሐፍ ቅዱሳችንን ከጻፉት ብዙ ነቢያት ጋር በመሠረታዊ ጉዳዮች የተለየ ነው። መሐመድን ከሚቃረናቸው ከመጽሐፍ ቅዱስ ጸሐፊዎች በላይ እንድናምነው የሚያደርግ ምንም ዓይነት በቂ ማስረጃ ያለው ምክንያት የለም።
4. ቁርዓን ከመለኮታዊ ምንጭ ስለ መገኘቱ ምንም በቂ ማስረጃ የለም።
5. የዐረብ ክርስቲያኖች አላህ የሚለውን ስም የመጽሐፍ ቅዱሱ እግዚአብሔር የዐረብኛ ቃል ትርጉም አድርገው ይጠቀሙበታል። በዚያ ውስጥ ኤሎሔ ወይም ቲዮስ (እግዚአብሔር) ሁሉም ቦታ አላህ ተብሎ ተተርጉሟል። ይህ ደግሞ እስልምና ከመጀመሩ በፊት የተደረገ ነው።

ይህም የሚያስከትለው ነገር አለ፡-

የመሐመድ ‹የያህዌ ኤሎሔ› ነቢይ ካልነበረ፥ መጽሐፉ-ቁርዓንም
ከእግዚአብሔር አይደለም ማለት ነው።
(የሚያስከትሉትን ውጤቶች ተመልከት!)

በቁርዓን የተገለፀው የአላህ መገለጥ፥ ባሕርይና ገጽታ ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር የማይገጥም ከሆነ የቁርዓኑ አላህ የአብርሃም፥ የይስሐቅ፥ የያዕቆብና የእስራኤል አምላክ፥ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አባት የሆነው እግዚአብሔር አይደለም ማለት ነው።

## የቁርዓኑ አላህ ማነው?

ቁርዓን መሐመድ እንዲህ እንዲል ይፈቀድለታል፡-

ሱረቱ 27፡ 91፡- የታዘዝኩት የዚህችን አገር ጌታ
ያንን ከ ልል ያደረጋትን
እንድገዛ ብቻ ነው፤ ነገሩም
ሁሉ የእርሱ ነው፤ ከሙስሊሞችም
እንድሆን ታዝዣለሁ (በላቸው)።

ከታሪክ እንደምንረዳው ሁባል የመካ ጌታ ሲሆን፥ አላህ ተብሎ ይጠራ ነበር። በሌላ ክፍል ስናነብ፡-

ሱረቱ 106 ፡- 3. የዚህን ቤት (የካዕባን) ጌታ ያምልኩ።

ይህ ቤት የተባለው ካዕባ በመካ መሐል ቆሞ ለረጅም ዘመናት ሁባልን ሲያስተናግድ ቆይቷል። ካዕባ በመጀመሪያ በአዳም ቆመ፥ በኋላም በአብርሃምና በእስማኤል እንደገና ተገነባ የሚለው የሙስሊሞች እምነት ምንም ዓይነት ታሪካዊ ማስረጃ የሌለው ባዶ ክርክርና ምኞታዊ አስተሳሰብ ነው። ካዕባ የአረማውያን መቅደስ የነበረ ነው።

## ሁባል ማን ነው?

አረማዊ በነበሩት ዐረቦች ዘንድ ብዙ አማልክት ይመለኩ ነበር። በቁርዓን ውስጥ ሦስት ሴት ‹አማልክት› በስም ተጠቅሰዋል። እነሱም፥ ላት፥ ዑዛ እና መናት ናቸው። (ሱረቱ 53፡19-20) እነዚህ የአላህ ሴት ልጆች ተብለው ይጠሩ ነበር (አት-ጠባሪ:- «ጂሚአል-በያን ፊጣፈሲር አል-ቁርዓን ቅጽ 27 ገጽ 34-36፥ እንዲሁም በሱረቱ 16፡57 እና 37፡149፥ 153 እንደተመለከተው)። በአምር ኢብን ሉሃድይ አገላለጽ መሠረት «ጌታ (አላህ ማለት ነው) በበጋ ከአል-ላት ጋር፥ በክረምት ደግሞ ከአል-ዑዛን ጋር ይኖራል» (ኤፍ፥ ቨስተን ፌልድ ዉዩኢስተን ፌልድ «የመካ ገድሎች»)። እነዚህና ሌሎችም ይኖራሉ ተብሎ በታመነባቸው በተለያዩ የአምልኮ ድንጋዮች (ዋታም) ውስጥ ይመለኩ ነበር።

«ስናም» የሚባሉም ደግሞ ነበሩ። እነዚህ በመሠረቱ የቲቀረጹ ምስሎች ናቸው። ስለ ሦስቱ የተቀረጹ ምስሎች የምናውቀው ነገር አለ። ሁለቱ ኢሣፍና እና ና›ኢላህ የሚባሉ ሲሆኑ በካዕባ የነበሩ በጣም የሚቀራረቡ ወጣት ፍቅረኞች እንደነበሩና መጨረሻም ወደ ድንጋይነት እንደተቀየሩ ይታመናል። ከዚያ በኋላ የሁለቱ የድንጋይ ምስሎች ለካዕባ በጣም ቅርብ በሆኑ በሁለት ኮረብታዎች (በሳፉ እና በማርዋ) ተቀመጡ። ሦስተኛው ምስል ደግሞ ሁባል ነበር።

ምናልባት ሁባል በመካ ውስጥ ‹በአይትሁ ›አላህ› ካዕባ ተብሎ በተጠራው «በአላህ ቤት» የነበረ ብቸኛ የተቀረጸ ምስል ሳይሆን አይቀርም። ይህ ምስል ከቆርኒሊያን (ቀይ የከበረ ድንጋይ) በሰው መልክ የተቀረጸው ነበር። አንዱ እጁ ተሰባብሮ በብር ተተክቶ እንደተሠራ ይታያል።

በእስልምና አፈ ታሪክ መሠረት ሁባል ከመሐመድ ጥቂት ቀደም ብሎ አረማዊ በነበረው በአመር ኢብን ቡሃአይ አማካኝነት ከሞአብ ወይም ከከለዳውያን ወደ ዐረብ ምድር እንደመጣ ይነገራል፤ («ኪታብ አልአድናም» በኢብን አል-ካልቢ ገጽ 23 እና «ሱረቱቱል ራሱል» ቁጥር 51)። ሆኖም ግን ስሙ ከ600 ዓመታት በፊት በ «ናባትሲያን ጽሑፎች» ተጠቅሶ ነበር። (ኤ.ቢ.ኩክ፤ «የሰሜን ሴማዊ ጽሑፎች» ገጽ 80፥ 158 እና «የሰሚቶ የጽሑፍ ስብስቦች» ገጽ 88፥ 117፥ 179፥ 182)።



ሁባል የሚለው ስም ትርጉም ምንድነው? ከዐረብኛው ቋንቋ ለማብራራት አይቻልም፤ («የእስልምና ኢንሣይክሎፒዲያ» በጊብ እና በክራመርስ)። ፐኮክ የተባለው ጸሐፊ «ስፔሲመን ሒስቶሪከ ዐረቡም» በተባለው መጽሐፉ ይህ ስም ምናልባት ሐ-በዓል ከሚለው የመጣ እንደሆን ሐሳብ ሰጥቷል። በጥንት የዕብራይስጥና የዐረብ የጽሑፍ ቋንቋ ላይ አናባቢ ድምጾች አይጻፉም ነበር። ስለዚህ ይህም ከተለመዱት ለውጦች አንዱ ሊሆን ይችላል፤ (ለምሣሌ:- አንድ ሰው መሐመድ፥ የሚለውን ስም ሙሐምድ፥ ማሐመት ወዘተ ብሎ ሊያነብ ይችላል)። በዕብራይስጥ «ሐ» ማለት «ኡ» የሚለው ገላጭ አናባቢ ሲሆን «ሐ-በዓል»ን በቀላሉ «በዓል» ብለን ልንጠራው እንችላለን። በብሉይ ኪዳን በዓል የሚባለውን ታስታውሳለህ? ሁባል ከሞአብ መምጣቱን የሚናገረው ሐሳብ የግምታችንን እውነተኛነት ከፍ ያደርገዋል።

> «እስራኤልም በሰጢም ተቀመጡ፤ ሕዝቡም ከሞዓብ ልጆች ጋር ያመነዝሩ
> ጀመር። ሕዝቡንም ወደ ምላኮቻቸው መሥዋዕት ጠሩ፤ ሕዝቡም በሉ፤ ወደ
> አምላኮቻቸውም ሰገዱ። እስራኤልም ብዔል ፌጎርን ተከተለ፤
> የእግዚአብሔርም ቁጣ በእስራኤል ላይ ነደደው፤» (ዘኁልቁ 25፡1-3)።

ጂ ዌልሐውሰን «ሬስቲ አረቢስቼን ሐጺንትሱምስ» በተባለው መጽሐፍ «አላህ ከመሐመድ በፊት የካዕባ ጌታ እንደነበር ታይቷል። ይህ የአምልኮ ቦታ ደግሞ ምስሉ ውስጡ ለተቀመጠው ለሁባል የተሰጠ እንደሆነ ሙሉ በሙሉ በእርግጠኝነት መናገር ባይቻልም ግምታችን በፍጹም ከእውነት የራቀ አይደለም» ብሏል (ገጽ 221)።

«አስቀድሞ መሐመድ በኋላም ተቃዋሚዎቹ እንደሚቀበሉት እውነት ከሆነ አላህ የካዕባ ጌታ ነው። ምናልባት አላህ የመካው ሁባል ይሆን? በሌላ አባባል፥ በእስራኤል ያህዌ አምላክ ኤሎሒ ተብሎ እንደተጠራው ሁባል በመካ አላህ ተብሎ ተጠርቶ ይሆን? ብለው ይጠይቃሉ። ጂ ዌልሐውሰን (በመጽሐፋቸው ገጽ 75)። በዓረብ ምድር የሚኖሩ ብዙ አማልክትን የሚያመልኩ ሰዎች አላህን እንደፈጣሪ ማወቃቸውን (ሱረቱ 23፡84-89፤ 26፡61)፥ በእርሱም እንደሚምሉ፤ (ሱረቱ 6፡109) ስንመለከት ደግሞ፥ የግምቱን እውነተኛነት ከፍ ያደርገዋል። ስለዚህ በመጀመሪያ አላህ የሚለው ስም እንደ ማዕረግ የሚያገለግል መሆን አለበት። «በመጀመሪያ አላህ የሚለው ስያሜ እያንዳንዱ ሰው የነገዱን አምላክ በመደበኛ ስሙ በመጥራት ፋንታ የሚጠቀምበት የአማልክቱ ሁሉ የጋራ ስም ነበር። ሁሉም ‹አላህ› ይላል፤ ግን እያንዳንዱ የራሱን አምላክ በልቡ ያስባል። ‹አምላክ› (አል-ኢላህ) የሚለው አገላለጽ ብቸኛ መጠቀሚያ ሆኖ፥ ሁሉም ነገሮች አንድ የጋራ አምላክ አላቸው ወደሚለው ሐሳብ ለመሸጋገር እንደ ድልድይ ሆኖ አገልግሏል።

አብዛኞቹ ምሁራን እንደሚስማሙበት አላህ የሚለው ስም ከ ‹አል-ኢላህ› እና/ወይም ከ ‹አል-ሊአህ› የመጣ ነው። ‹ኢል-ኢላህ› ከሌሎች ጋር ሲወዳደር ‹አምላክ› ማለት ሲሆን፥ ‹አል-ሊአህ› ደግሞ ‹የሚመለክ› ማለት ነው።

ሆኖም ግን በብሉይ ኪዳን እግዚአብሔር ተብሎ ከተተረጎመው ‹ኢላህ› ከሚለው የዕብራይስጥ ቃል ጋር የቅርብ የሆነ መመሳሰል አለው። (89 ጊዜ ከ ‹ኤል› ጋር ተወዳድሯል 224 ጊዜ፤ እንዲሁም ኤሎሒ 3251 ጊዜ።

ከመሐመድ በፊት የመጽሐፍ ቅዱስ የተወሰኑ ክፍሎች በዐረብኛ እንደተተረጎሙ ለማመናችን ምክንያት አለን። በነዚህ ላይ ቲዮስ ወይም ኤሎሒ፥ ወዘተ የሚለው ስም አላህ ተብሎ ተተርጉሞ ነበር። ከላይ የተጠቀሱትን ሁሉ ከግምት ውስጥ በማስገባት፥ በአይሁዶችና በክርስቲያኖች የአንድ አምላክ አምልኮ ተፅዕኖ ሥር የነበረውን የቅድመ እስልምና ፅንሰ-ሐሳብ ስናየው ብዙዎቹ አማልክት በአንድ ተተክተው የቁርዓን አላህ ብቅ እንዳለ መገመቱ፥ እውነትነት ያለው ነገር ነው።

ነገር ግን እስቲ የኢብን ኢስሐቅ በሆነው በ ‹ሲራቱል ራሱል› («የነቢዩ ሕይወት») ውስጥ የተገለጸውን ሁባልን እንመልከት። «የነቢዩ ሕይወት» በጣም ጥንታዊ የሆነው የመሐመድ ታሪክ ነው። ኢብን ኢስሐቅ ከሒጅራ በኋላ በ85 ዓመት ተወለደ፤ (ሂጅራ በ622 ዓ.ም. ነው የተፈጸመው)። ከዚያ በኋላ ይህን የሕይወት ታሪክ ጽሑፍ ብዙ ምንጮችን በመጠቀም ጻፈ። ይህ ጽሑፍ አሁን ጠፍቷል፥ ነገር ግን በኢብን ሐሻም ተሻሽሎ የተጻፈው እስከዛሬ ተጠብቆ ተቀምጧል።

## ‹አብዱል-ሙታሊብ› ወንድ ልጁን ለመሠዋት የገባው ቃል ኪዳን ተቀባይነት አግኝቷል።

ሆኖም እግዚአብሔር ብቻ ነው እውነቱን የሚያውቀው። አብዱል-ሙታሊብ ዘምዘማን በሚቆፍርበት ጊዜ በድንገት የቁራይሽ ተቃውሞ አጋጠመ። በዚህም ጊዜ አሥር ልጆች ኖረውት አድገው ቢከላከሉለት አንዱን በካዕባ ለእግዚአብሔር መሥዋዕት አድርጎ ሊያቀርብ ቃል ገባ። ከዚያ በኋላ ሊከላከሉለት የሚችሉ አሥር ልጆች ካደረሰ በኋላ፥ ሰበሰባቸውና ስለገባው ቃል ኪዳን ነግሯቸው፥ በእግዚአብሔር ላይ እምነታቸውን እንዲያጸኑ ነገራቸው። እነርሱም አባታቸውን ለመታዘዝ ተስማምተው ምን ማድረግ እንዳለባቸው ጠየቁት። እርሱም እያንዳንዳቸው ቀስት ፈልገው ስማቸውን በቀስቱ ላይ ጽፈው ወደ እርሱ እንዲያመጡ ነገራቸው። ይህንኑ ካደረጉ በኋላ በካዕባ መሐል



ወዳለው ወደ ሁባል ፊት አመጣቸው። የሁባል 2 ምስል በኩሬው ዳር ቆሞ ነበር። በካዕባ የሚሰጡ ስጦታዎች ሁሉ በዚያ ውስጥ ነበር የሚከማቹት።

እያንዳንዳቸው ጥቂት ቃላት የተጻፉባቸው ሰባት ቀስቶች በሁባል አጠገብ ተቀምጠዋል። አንዱ ‹የደም ዕውቀት› ተብሎ ተጽፎበታል። የደሙን ክፍያ ማን መክፈል እንዳለበት ክርክር ሲነሣ፥ በሰባቱ ቀስቶች እጣ ይጣጣሉና ዕጣው የደረሰው ሰው ገንዘቡን መክፈል ነበረበት። ሌላው ‹አዎን› የሚል ተጽፎበታል። ሌላው ደግሞ ‹አይደለም› የሚል ተጽፎበታል። እንግዲህ በነገሩ ላይ ስለወደፊቱ በተነገረው ቃል መሠረት ያደርጋሉ ማለት ነው። ሌላው ቀስት ‹የእናንተ› ተብሎ ተጽፎበታል፤ ሌላው ‹ሙልሳቅ› 3፤ ሌላው ‹የአንተ አይደለም›፤ የመጨረሻው ደግሞ ‹ውኃ› ተብሎ ተጽፎባቸዋል።

ምናልባት ውኃ በማውጣት መቆፈር ቢፈልጉ ይህንን ቀስት ይዘው ዕጣዎች ይጥሉና ዕጣው በወጣበት ሥፍራ ለመስራት ይዘጋጃሉ። ምናልባት ወንድ ልጅን መግረዝ፥ ጋብቻ መፈጸም፥ ወይም ሬሣ መቅበር ቢፈልጉ፥ ወይም የአንድን ሰው የዘር ሐረግ ቢጠራጠሩ ወደ ሁባል ከመቶ ዲርሐም (ብር) ጋር በመውሰድ ግመል ያርዱና ዕጣውን ለጣለው ሰው ይሰጡታል። ከዚያም ጉዳዩ ወደሚመለከተው ሰውዬ፥ «አምላካችን ሆይ የ ‹እንትና› ልጅ ከሆነው ከ ‹እገሌ› ጋር እንዲህና እንዲህ ለማድረግ አስበናል፤ ስለዚህ ስለ እርሱ ትክክለኛውን መንገድ አሳየን» በማለት ይቀርባሉ። ከዚህ በኋላ ሰውዬውን «ዕጣውን አውጣ!» ይሉታል። በዚህ ጊዜ «የእናንተ» የሚለው ቀስት ከወጣ ሰውዬው የነገዳቸው ትክክለኛ ዘር ነው ማለት ነው። ነገር ግን «የእናንተ አይደለም» የሚለው ከወጣ ከነርሱ ጋር በቃል ኪዳን የተስማማ ነው ማለት ነው። ‹ሙልሳቅ› የሚለው ከወጣ ደግሞ ከነርሱ ጋር ምንም የሥጋ ዝምድና የሌለው በቃል ኪዳንም ያልተስማማ ነው ማለት ነው። በሌሎች ጉዳዮች ላይ ‹አዎን› የሚለው ሲወጣ እንደዚያ ያደርጋሉ። መልሱ ደግሞ ‹አይደለም› የሚለው ከሆነ ነገሩን እንደገና እስኪያመጡት ድረስ ለአንድ ዓመት ይተዉታል። ጉዳዮቻቸውን ሁሉ የሚወስኑት በቀስቶቹ መሠረት ነበር።

አብዱል-ሙታሊብ ቀስቱን ለያዘው ሰውዬ «ስለ ልጆቼ በእነዚህ ቀስቶች ዕጣ ጣል» አለው። ስለገባውም ቃል ኪዳን ነገረው። እያንዳንዱ ልጅ ስሙ የተጻፈበትን ቀስት ለሰውዬው ሰጠ። አብዱላህ የአባቱ የመጨረሻ ልጅ ነበር። እሱና አል-ዙባይር እንዲሁም አቡ ጣሊቅ ለፋጡማ ተወለዱላት። ፋጡማ ለዓሚር (አሚር ለአይድ ለአብዲ ለኢምራን ለማቅሕዙም ለያቃዛ ለሙራ ለቃዓብ ለሉዓይ ለጋሊብ ለፈህር ተወለዱ 113)። እንደሚታመነው አብዱላህ

የአብዱል-ሙታሊብ በጣም ተወዳጅ ልጅ ስለነበር፣ አባቱ የሱ ቀስት ሳይወጣ ቀርቶ ልጁ እንደሚድን አስቦ ነበር። (እሱ የእግዚአብሔር መልእክተኛ አባት ነበር)። ሰውዬው ዕጣውን ከነርሱ ጋር በሚያወጣበት ጊዜ አብዱል-ሙታሊብ ከሁባል አጠገብ ቆሞ ወደ አላህ ይጸልይ ነበር። ከዚያም ሰውዬው ዕጣውን ሲያወጣ የአብዱላህ ቀስት ወጣ። አባትዬውም ትልቅ ቢላ ይዞ ልጁን እየመራ መሄድ ጀመረ። ከዚያም ሊሠዋው እስከ ኢሳፍና ነኢላ (ቲ. መሥዋዕታቸውን የሚያርዱበት የቀራዮሽ ሁለት ጣዖታት) ድረስ አመጣው። ነገር ግን ቁራይሽ እና ልጆቹ ከመሰብሰቢያቸው ወጡና ምን ሊያደርግ እንዳሰበ ጠየቁት። ልሠዋው ነው ባላቸው ጊዜ እንዲህ አሉት:- ‹በእግዚአብሔር ይሁንብህ! ታላቁን የመቀጫ መሥዋዕት ለእርሱ እስከታቀርብለት ድረስ በፍጹም እንዳትሠዋው። አንተ እንዲህ ዓይነቱን ነገር ብታደርግ ሰዎች ልጆቻቸውን እያመጡ ከመሠዋት የሚያግዳቸው ምንም አይኖርም። ይህ ደግሞ ለሰዎች ሁሉ እንዴት ይሆናል?› ከዚያም እንዲህ አሉ:- የአል-ሙግሐሬ የአብድላህ ልጅ የአምር የማክህዘም ልጅ የያቃዛ ልጅ ‹ከሱ ነገድ የሆነችው የአብዱላህ እናት:- ‹በእግዚአብሔር› ታላቁን የመቀጫ መሥዋዕት እስከታቀርብለት ድረስ በፍጹም እንዳትሠዋው። ምንም እንኳ የቤዛው ክፍያ ንብረታችን በሙሉ ቢሆንም እንዋጀዋለን። ቆሪዩሽና ልጆቹ ይህን ማድረግ እንደሌለበት ነገሩት፤ ነገር ግን የውቃቢ መንፈስ ያለባትን ሒጃዝ1 የተባለችው ጠንቋይ ጋ ሄዶ እሷን እንዲያማክራት ነገሩት። ከዚያ በኋላ ለሚያደርገው ነገር ሁሉ ነፃነት እንዳለው ነገሩት። እሷ ልጁን እንዲሠዋ ከነገረችው ከዚያ የበለጠ ምንም ማድረግ አይችልም፤ ሌላ መልካም ምላሽ ከሰጠችውም ያንኑ መቀበል አለበት። ከዚያ የመዲና ያህል ርቀት ከተጓዙ በኋላ በቀይባር እንደሆነች አወቁ። ጉዞአቸውንም ቀጠሉ። እስኪያገኟት ድረስ ከጋለቡ በኋላ አብዱል-ሙታለብ ነገሩን ሁሉ ገለጠላት። እሷም ውቃቢዋ እስኪመጣና እስከትጠይቀው ድረስ እንዲሄዱ ነገረቻቸው። ይህን ሰምተው ከሷ ሲሄዱ አብዱል-ሙታሊብ ወደ አላህ ጸለየ። ከዚያም በነጋታው ተመልሰው ሲመጡ እንዲህ አለች፥ «አንድ ቃል መጥቶልኛል (ተገልጦልኛል)፤ በእናንተ ዘንድ የደም ገንዘብ ምን ያህል ነው?» እነሱም በእርግጥ አሥር ግመሎች ናቸው አሏት። ከዚያም ወደ ሀገራቸው ተመልሰው፥ ከአሥሩ ግመሎች ጋር ወጣቱን ልጅ እንዲወስዱና ለሁለቱ ዕጣ እንዲጥሉ ነገረቻቸው። ዕጣው በልጁ ላይ ከደረሰበት፥ ጌታችሁ በቃኝ እስኪል ድረስ ሌሎች ግመሎች ጨምሩ። ነገር ግን ዕጣው በግመሎቹ ላይ ከወደቀ፥ ጌታችሁ ረክቷልና በልጁ ፋንታ ግመሎቹን ሠዉ። ልጁም ከሞት ይድናል አለቻቸው። ከዚያም ወደ መካ ተመልሰው የተነገራቸውን መመሪያ ሊፈጽሙ ሲሉ አብዱል-ሙታሊብ ወደ አላህ ይጸልይ



ነበር። ከዚህ በኋላ አብዱል-ሙታሊብ ከሁባል አጠገብ ቆሞ ወደ አላህ ሲጸልይ ሳለ፥ አብዱላህና አመር ግመሎችን አመጡ። ከዚያም ዕጣውን ሲያወጡ ቀስቱ ወደ አብዱላህ ላይ አመለከተ (ወጣበት)። እንደገና አሥር ግመሎች በበፊቶቹ ላይ ጨምረው ዕጣ ሲጥሉ፥ አሁንም በአብዱላይ ላይ ወጣ። ከዚያም በእያንዳንዱ የዕጣ ማውጣት ጊዜ አሥር አሥር ግመሎት እየጨመሩ ማውጣት ቀጠሉ። በመጨረሻ ግመሎቹ መቶ ሲደርሱ ዕጣው በነርሱ ላይ ወደቀ። ቁሬዮሽና ከእርሱ ጋር የነበሩት ‹አብዱል-ሙታሊብ በመጨረሻ ጌታህ የሚያረካውን አግኝቷል› አሉት። ‹በእግዚአብሔር እንዲህ አይደለም› ብሎ መለሰላቸው። (እነሱ እንደሚሉት) ‹ዕጣውን ሦስት ጊዜ እስከሚወጣ ድረስ አይሆንም› አላቸው። ይህንኑ አደረጉ። ሦስቱንም ጊዜ ዕጣው በግመሎቹ ላይ ወጣ። በመጨረሻ በደንቡ መሠረት ከታረዱና ከተቀመጡ በኋላ ማንም ሰው ከመብላት አልተከለከለም (114)።

## ማስተዋል ያለብን ነገር:-

1. አብዱል-ሙታሊብ የመሐመድ አያት ሲሆን፥ አብዱላህ ደግሞ አባቱ ነው፤ (አብ-ደላህ ማለት የአላህ አገልጋይ ማለት ነው።)
2. አንዱ የአብዱል-ሙታሊብ ልጅ ‹ለእግዚአብሔር በካዕባ› መሠዋት ነበረበት።
3. አሁን እንዳየነው የካዕባ አምላክ ሁባል ነበር።
4. ለግርዘት፥ ለጋብቻ፥ ለቀብር ወዘተ ሰዎች ‹የዚህ ቤት ጌታ› ወደ ሆነው ወደ ሁባል ይሄዱ ነበር።
5. የሁባልን ፈቃድ ለማወቅ ጥንቆላን ይጠቀሙ ነበር፤ (በቀስት ዕጣ በመጣጣል)።
6. አብዱላህ የተባለው ልጅ ሊሠዋ ወደ ጣዖቱ (ወደ ሁባል-አላህ) ቀርቦ ነበር።
7. አብዱል-ሙታሊብ የውቃቢ መንፈስ የነበረባትን ጠንቋይ አማከሯል። (እንደ አክስፎርድ መዝገበ-ቃላት ገለጻ አጋንንት የሚመጡለትና የሚታዘዙለት አስማተኛ»)።
8. በጥንቆላ በኩል ከባለውቃቢዋ መንፈስ መልስን አግኝቷል።
9. «ጌታው እስኪረካ ድረስ» በሁባል ፊት ዕጣ መጣል ነበረበት። ይህ ጌታ ሊሆን የሚችለው ሁባል-አላህ ብቻ ነው።

## ከዚህ የምንገነዘበውና የምንማረው ምንድነው?

መሐመድ አጥብቆ አንድ አምላክን የሚያመልክ ስለመሆኑ ምንም ጥያቄ የለንም። ሁባልን ጨምሮ ሁሉንም ጣዖታት አጥፍቷል። አላህን ብቻ ‹እንዲቆይ› በመፍቀድ፥

«እኔ፥ እኔ ነኝ፤ የአብርሃም፥ የይስሐቅና የያዕቆብ አምላክ ነኝ» ካለው ጋር አንድ አድርጎ አቅርቦታል።

ነገር ግን «የዚህች ከተማ ጌታ» (ቃዕባ ማለት ነው) «የዚህ ቤት ጌታ» ከላይ እንደተመለከትነው ከሁባልና ከሞላ ጎደል ከዓረብ አማልክት ድምር ጋር ተስተካክሎ የቀረበው አላህ እግዚአብሔር አይደለም።

> «አንተ፥ እግዚአብሔር፥ በምድር ሁሉ ላይ ልዑል ነህና፥ በአማልክትም ሁሉ ላይ እጅግ ከፍ ከፍ ብለሃልና» (መዝ. 97:9)።

**ዋናው ቁም ነገር ሙስሊሞች ማንን እንደሚያመልኩናለማን ራሳቸውን እንደሰጡ የሚያስቡት አሳብ ሳይሆን፥ በተጨባጭ የሚሰግዱለት ማን መሆኑን ነው!**

## እግዚአብሔር እና አላህ

እስቲ የሁለቱን ባሕርይና ተፈጥሮ እናወዳድር

እግዚአብሐር፡- አንድ አምላክ ነው ነገር ግን በሥላሴነት ተገልጧል («እስልምና ስለ ራሱ ያለው አመለካከት፥ ሌሎች ያላቸው አመለካከትና ምንነቱ ገጽ 67)

የሦስትነቱ ክፍል እግዚአብሔር ወልድ ተብሎ የሚጠራው ጌታ ኢየሱስና እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ናቸው። ይህንንም ያለምንም ቅሬታ ነው የምንገልጸው። በመጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር ራሱን የገለጠው እንዲህ ነውና።

አላህ፡- ‹ውሉድ› ነው፤ ማለትም አንድነትም፥ ነጠላነትም አለው።

ሰረቱ 5፡ 75፡- የመርየም ልጅ አልመሲሕ
ከበፊቱ መልእክተኞች በእርግጥ
ለፈ የሆነ መልእክተኛ እንጂ
ሌላ አይደለም፤ እናቱም
በጣም እውነተኛ ናት (ሁለቱም)
ምግብን የሚበሉ ነበሩ። ዐንቀጾችን
ለነርሱ (በከሐዲዎች) እንዴት
እንደምናብራራ ተመልከት፤



ከዚያም (ከእውነት) እንዴት
እንደሚመለሱ ተመልከት።

76፡- ከአላህ ሌላ ለናንተ መጉዳትንና
መጥቀምን የማይችልን ትገዛላችሁን?
በላቸው፤ አላህም እርሱ ሰሚው
አዋቂው ነው።

78፡- ከእስራኤል ልጆች እነዚያ የከዱት
በዳውድና በመርያም ልጅ በዒሣ
ምላስ ተረገሙ፤ ይኸ ትዕዛዝን
በመጣኋቸውና ወሰንን የሚያልፍ
በመሆናቸው ነው።

ሱረቱ 4፡- 171፡- እላንተ የመጽሐፍ ሰዎች ሆይ!
በሃይማኖታችሁ ወሰንን አትለፉ፤
በአላህም ላይ እውነትን እንጂ ሌላ
አትናገሩ፤ የመርየም ልጅ አል
መሲሕ ዒሣ የአላህ መልእክተኛ
መርያም የመጣላት (የሆነ)
ቃሉም ከእርሱ የሆነ መንፈስ
ብቻ ነው፤ በአላህን
በመልእክተኞቹም እመኑ፤
(አማልዕክት) ሦስት ናቸው
አትበሉም፥ ተከልከሉ፥ አላህ
አንድ አምላክ ብቻ ነው።
በርሱ ልጅ ያለው ከመሆን የጠራ
ነው። በሰማያትና በምድር ያለ
ሁሉ የርሱ ነው። መኪያም
በአላህ በቃ።

ሰረቱ 19፡- 35፡- ለአላህ ልጅን መያዝ
አይገባውም፤ (ከጉድለት ሁሉ)
ጠራ፤ ነገርን በሻ ጊዜ ለእርሱ
የሚለው ኹን ነው፤ ወዲያውም
ይሆናል።

ሱረቱ 9:- 30:- አይሁድ ዑዘይር የአላህ ልጅ
ነው አለች፤ ክርስቲያኖችም
አልመሲሕ የአላህ ልጅ ነው አሉ፤
በአፎቻቸው የሚናገሩት
ቃላቸው ነው፤ በዚህም) የእነዚያን
ከነሱ በፊት የካዱትን ሰዎች ቃል
ያመሳስላሉ፤ የአላህ መርገም
በላያቸው ላይ ይሁን፤ ምን ያህል
ከእውነት ፈቀቅ ብለዋል!

እግዚአብሔር:-

እጅግ በጣም ዋነኛ የሆነው የእግዚአብሔር ባሕሪይ ምንድነው? ተብሎ ቢጠየቅ፤ አብዛኛው ክርስቲያን ባለማወላወል (ፍቅር) ብሎ ይመልሳል። ከእግዚአብሔር ቃል ጥቂት ቦታዎች እንኳን ብንጠቅስ ይህን በሚያሳምን ሁኔታ ያረጋግጣሉ።:- «እግዚአብሔርም ከሩቅ ተገለጠልኝ እንዲህም አለኝ:- በዘላለም ፍቅር ወድጄሻለሁ ስለዚህ በቸርነት ሳብሁሽ» (ኤር. 31:3)።

«እርሱም:- በእውነት ሕዝቤ ሐሰትን የማያደርጉ ልጆች ናቸው አለ፤ መድኃኒትም ሆነላቸው። በጭንቃቸው ሁሉ እርሱ ተጨነቀ፥ የፊቱም መልአክ አዳናቸው፤ በፍቅሩና በርኅራኄውም ተቤዣቸው፥ በቀደመውም መን ሁሉ አንሥቶ ተሸከማቸው» (ኢሳ. 63:8-9)።

«በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዷልና። ዓለም በልጁ እንዲድን ነው እንጂ በዓለም እንዲፈርድ እግዚአብሔር ወደ ዓለም አልላካቸውምና» (ዮሐ. 3:16-17)።

«ኢየሱስም ከፋሲካ በዓል በፊት ከዚህ ዓለም ወደ አብ የሚሄድበት ሰዓት እንደደረሰ አውቆ፥ በዚህ ዓለም ያሉትን ወገኖቹን የወደዳቸውን እስከ መጨረሻው ወደዳቸው።» (ዮሐ. 13:1)

«አብ እንደወደደኝ እኔ ደግሞ ወደድኋችሁ፤ በፍቅሬ ኑሩ። እኔ የአባቴን ትእዛዝ እንደጠበቅሁ በፍቅሩም እንደምኖር፥ ትእዛዜን ብትጠብቁ በፍቅሬ ትኖራላችሁ። ደስታዬም በእናንተ እንዲሆን ደስታችሁም እንዲፈጸም ይህን ነግሬአችኋላሁ። እኔ እንደወደድኋችሁ እርስ በርሳችሁ ትዋደዱ ዘንድ ትእዛዜ ይህች ናት» (ዮሐ. 15:9-12)።



«ነገር ግን እግዚአብሔር በምሕረቱ ባለጠጋ ስለሆነ:- ከወደደን ከትልቅ ፍቅሩ የተነሣ በበደላችን ሙታን እንኳ በሆንን ጊዜ ከክርስቶስ ጋር ሕይወት ሰጠን፤ በጸጋ ድናችኋልና» (ኤፌ. 2:4-5)።

«ገና ደካሞች ሳለን ክርስቶስ ዘመኑ ሲደርስ ስለኃጢአተኞች ሞቷልና። ስለ ጻድቅ የሚሞት በጭንቅ ይገኛልና፤ ስለ ቸር ሰው ግን ሊሞት እንኳ የሚደፍር ምናልባት ይገኝ ይሆናል። ነገር ግን ገና ኃጢአተኞች ሳለን ክርስቶስ ስለ እኛ ሞቷልና እግዚአብሔር ለእኛ ያለውን የራሱን ፍቅር ያስረዳል» (ሮሜ 5:6-8)።

«ከክርስቶስ ፍቅር ማን ይለየናል? መከራ፥ ወይስ ጭንቀት፥ ወይስ ስደት፥ ወይስ ራብ፥ ወይስ ራቁትነት፥ ወይስ ፍርሃት ወይስ ሰይፍ ነውን? ስለ አንተ ቀኑን ሁሉ እንገደላለን እንደሚታረዱ በጎች ተቆጠርን ተብሎ እንደተጻፈ ነው። በዚህ ሁሉ ግን በወደደን በእርሱ ከአሸናፊዎች እንበልጣለን። ሞት ቢሆን፥ ሕይወት ቢሆን፥ መላእክትም ቢሆኑ፥ ግዛትም ቢሆን፥ ያለውም ቢሆን፥ የሚመጣውም ቢሆን፥ ኃይላትም ቢሆኑ፥ ከፍታም ቢሆን፥ ዝቅታም ቢሆን፥ ልዩ ፍጥረት ቢሆን በክርስቶስ ኢየሱስ በጌታችን ካለ ከእግዚአብሔር ፍቅር ሊለየን እንዳይችል ተረድቼአለሁ» (ሮሜ 8:35-39)።

«ከክርስቶስ ጋር ተሰቅዬአለሁ፤ እኔም አሁን ሕያው ሆኜ አልኖርም፤ ክርስቶስ ግን በእኔ ይኖራል፤ አሁንም በሥጋ የምኖርበት ኑሮ በወደደኝና ስለ እኔ ራሱን በሰጠው በእግዚአብሔር ልጅ ላይ ባለ እምነት የምኖረው ነው» (ገላ 2:20)።

«የእግዚአብሔር ልጆች ተብለን ልንጠራ አብ እንዴት ያለውን ፍቅር እንደሰጠን እዩ፤ እንዲሁም ነን» (1 ዮሐ. 3:1)።

«ፍቅር የሌለው እግዚአብሔርን አያውቅም፤ እግዚአብሔር ፍቅር ነውና። በዚህ የእግዚአብሔር ፍቅር በእኛ ዘንድ ተገለጠ፤ በእርሱ በኩል በሕይወት እንኖር ዘንድ እግዚአብሔር አንድ ልጁን ወደ ዓለም ልኮታልና። ፍቅርም እንደዚህ ነው፤ እግዚአብሔር እርሱ ራሱ እንደወደደን ስለ ኃጢአታችን ማስተሰሪያ ይሆን ዘንድ ልጁን እንደላከ እንጂ እኛ እግዚአብሔርን እንደወደድነው አይደለም፤ እኛም እግዚአብሔር ለእኛ ያለውን ፍቅር አውቀናል አምነንማል። እግዚአብሔር ፍቅር ነው በፍቅርም የሚኖር በእግዚአብሔር ይኖራል። እግዚአብሔርም በእርሱ ይኖራል» (1 ዮሐ 4:8-10፥ 16)።

«እርሱ አስቀድሞ ወዶናልና እኛ እንወደዋለን» (1 ዮሐ. 4:19)።

«ለወደደን ከኃጢአታችንም በደሙ ላጠበን መንግሥትም፥ ለአምላኩና ለአባቱም ካህናት እንድንሆን ላደረገ፤ ለእርሱ ከዘላለም እስከ ዘላለም ድረስ ክብርና ኃይል ይሁን፤ አሜን» (ራዕ 1፡5፥6)።

‹ፍቅር› የሚለው ቃልና ተዛማጅ ቃላት በአዲስ ኪዳን (25% ከቁርዓን በሚሠፋው) ብቻ 250 ጊዜ መጠቀሱ እጅግ ጠቃሚ አይደለም? በአንጻሩብቁርዓን23 ጊዜብቻ ነው የተጠቀሰው። (ስለ አላህ የሚናገሩትን ቀጥለን እናያቸዋለን)።

አላህ፡-

ልክ እንደበፊቱ ሙስሊሞችን ደግሞ፥ እጅግ በጣም ዋነኛ የሆነው የአላህ ባሕሪይ ምንድነው? ብለን ብንጠይቃቸው፥ የሚነግሩን ነገር ‹አላሁ አክበር› - አላህ ታላቅ ነው! አላህ ኃይለኛ ነው! የሚለውን ነው። (ሱረቱ 3፡26፤ 6፡65፥ 102፤ 30፡54፤ 54፡55፤ 65፡12 ወዘተ)። እሱ ከሁሉ በላይ ሆኖ ብቻውን ደስ የሚያሰኘውን ሊያደርግ የሚችል ሉዓላዊ ነው። ሙሉ በሙሉ በምንም አይወሰንም።

አል-ግሃዛሊ የተባለው ዝነኛው የእስልምና ሥነ-መለኮት ምሁር (በ1000 ዓ.ም. ነው የሞተው፤) (የእስልምና መዝገበ ቃላት ‹አላህ› በሚለው ሥር - እንደአብራራው) እንዲህ ብሎ ነበር፡-

እርሱ በመጀመሪያ ለኃይሉ፥ ለፈቃዱ መግለጫ፥ ከዘላለም ዘመናት በፊት፥ እውነት ለሆነው ለቃሉ ማረጋገጫ ሁሉን ነገር ፈጠረ። አስፈልገውት ወይም ፈልጓቸው አይደለም። ነገር ግን እሱ በመፍጠር፥ በመሥራት፥ በማዘዝ፥ በምንም ነገር አስገዳጅነት ሥራ ሳይሆን፥ ምንም ሳያስፈልገው የራሱን ክብር በመግለጥና በማወጅ ፈጠራቸው። ፍቅርና ቸርነት፥ ውለታና ጸጋ፥ እንዲሁም መልካም ነገር ሁሉ ከእርሱ ናቸው። በሌላ በኩል ደግሞ በሰዎች ላይ ቁጣውንና መከራን ሊያፈስና በተለያየ ዓይነት ሐዘንና በሽታ ሊያሠቃያቸው ኃይል ችሎታ አለው። ምናልባትም እነዚህን ነገሮች ቢያደርግ አይከሰስም፤ ፍትሕ አጓድለሃል ተብሎም ሊጠየቅ አይችልም።

ደግሞም የሚያመልኩትንና የሚታዘዙትን ስለ ቃል ኪዳኑና ስለ በጎ ስጦታው ብድራታቸውን ይሰጣቸዋል። ይህንንም የሚያደርገው የሚገባቸውና ለርሱ ጠቃሚዎች ስለሆኑ አይደለም። እርሱ መፈጸም አለብህ ተብሎ የሚያዝበት ምንም ነገር የለምና። ምንም የፍትሕ መጓደል በእርሱ ላይ ሊታሰብ አይችልም። እርሱ በማንኛውም ሰው፥ በማንኛውም ሁኔታ ማድረግ አለብህ ተብሎ የሚገደድበት ምንም ነገር የለም። ይህ እንዲህ ሆኖ ሳለ የእርሱ ፍጡራን ግን



ሊያገለግሉት ይገባል። በነቢያቱ አፍ እንዳስታወቀው እነርሱ እሱን የማገልገል ጥብቅ ግዴታ አለባቸው።

በእኩል ደረጃ ታዋቂ የነበረው ቁርዓንን የሚያብራራው አል-ባርቃዊ ‹በተመሳሳይ መጽሐፍ› በዚህ ጉዳይ ላይ ሲያብራራ እንዲህ ብሏል፡-

ምንም ነገር ይሁን እርሱ ምንም አይጠቀምም፤ ምንም አይጎዳም። ሁሉም አማኞች ቢሆኑ፥ እንዲሁም ለክሕደታቸው በጣም ራሳቸውን የሰጡ ሃይማኖት የለሾች ከሐዲዎች ቢሆኑ፥ እርሱ ምንም አይጎድልበትም። የወደደውን መሥራት ይችላል፤ እርሱ የፈቀደውን ሁሉ ደግሞ ይፈጽማል። አንድም ነገር እንዲያደርግ አይገደድም። በዚህ ዓለም ያለ ሁሉ መጥፎም ሆነ ጥሩ ነገር የሚኖረው በእርሱ ፈቃድ ነው። የአማኙን እምነትና የሃይማኖተኛውን ቅድስና ይፈቅዳል።

ፈቃዱን ቢቀይር ኖሮ ማንም እውነተኛና ራሱን የሰጠ አማኝ ወይም ከሐዲ ሰው ሊኖር አይችልም ነበር። በተጨማሪም የማያምነውን ሰው ዓለማመንና የኃጢአተኞችን ሃይማኖት የለሽነት ይፈቅዳል።

ያለዚህ ፈቃድ ዓለማመንም ሆነ ሃይማኖት የለሽነት ሊኖሩ አይችሉም። እኛ የምናደርገው ነገር ሁሉ በእርሱ ፈቃድ ነው። የማይፈቅደው ነገር ሊደረግ በፍጹም አይችልም። አንድ ሰው ለምን አላህ ሁሉም ሰዎች እንዲያምኑ አይፈቅድም? ብሎ ቢጠይቅ የኛ መልስ፡- «አላህ ስለሚያደርገውና ስለሚፈቅደው ነገር ለመጠየቅ ምንም መብት የለንም። እርሱ አንድን ነገር ለመፍቀድና ደስ ያሰኘውን ለመሥራት ሙሉ በሙሉ ነፃ ነው» የሚል ነው። የማያምኑትን በመፍጠር በዚያው ዓለማመናቸው እንዲጸኑ በመፍቀድ አባብን፥ ዓሳማንና ሌሎች ክፉ ነገሮችን በመፍጠር አላህ የራሱ የሆነና እኛ ልናውቀው የማያስፈልግ መልካም ፍጻሜ አለው። የአላህ ፈቃድ ዘላለማዊ እንደሆነና ከማንነቱ በኋላ የመጣ እንዳልሆነ መረዳት አለብን።

በተደጋጋሚ ወደ ምሥራቅ አገሮች የሚጓዘውና የስልምና ምሁር የሆነው ሚስተር ፓልግሬቪ በተጨማሪ እንዲህ ብሏል፡-

ይህ መለኮታዊ ክስተት በሕዋ ሁሉ ውስጥ የሚገኝ፥ ብቸኛው ተወካይ፥ ብቸኛው ኃይል፥ ብቸኛው ድርጊት ነው። እርሱም ሌሎች ክስተቶች ሁሉ ቁስ አካላዊ ወይም መንፈሳዊ፥ የተፈጥሮ ዕውቀት ወይም የትምህርት ዕውቀት፥ ሥጋዊ ወይም ግብረ-ገባዊ፥ ምንም ሳያደርጉ ዝም ብለው ሁኔታዎችን እንዲቀበሉ (እንዲገዙ) ያደርጋቸዋል። በእንቅስቃሴ ወይም ረግተው በመቀመጥ፥ በተግባር ወይም በችሎታ ሁሉ ብቸኛው ኃይል፥ ብቸኛው ሞተር፥ እንቅስቃሴ፥ ጉልበትና ግብር አላህ ብቻ ነው። ሌላው እንዲኖሩ የሚፈቅድ ነው። ሁሉ ከከፍተኛው የመላዕክት አለቃ እስከ ዝቅተኛው ንጥተ-ነገር (አቶም) ድረስ፥ በተዋረድ የተቀመጠና በመሣሪያነት የሚያገለግል ነው።

በዚህ ዓይነት ሥነ-መለኮት ፍጹም ለሆነ መልካም ወይም መጥፎ ነገር፥ ለምክንያት ወይም ለብኩንነት ምንም ቦታ የለውም። ሁሉም ነገሮች በተዋረድ የተቀመጡ የታላቁ ተወካይ ድልድዮች ናቸው።

እንግዲህ ሊለካ በማይችልና በዘላለማዊ ክብር በላይ የከበረው፥ በአንድ ዓይነት መሠረት ላይ በተቀማጭነት ካሉት ፍጥረታት ሁሉ አምሳያ የሌለው፥ በሁሉን ቻይነት ሁሉን ነገር ጠቅልሎ የያዘውና በሁሉ ቦታ በመገኘት ሥራውን የሚሠራው አላህ አንድ ነው። ምንም ዓይነት ሕግ፥ መለኪያ፥ ወይም ወሰን ብቸኛ ከሆነው ፍጹም ፈቃዱ አያግዱትም። ለፍጥረቱ ምንም የሚያስተላልፍላቸው ነገር የለም፤ ምክንያቱም የሚታየው ኃይል ሁሉ የርሱ ብቻ ነው። እንዲሁም ከፍጥረቱ በምላሽ የሚቀበለው ምንም ነገር የለም። እነሱ ምንም ነገር ይሁኑ ሁሉ ለእርሱ በእርሱና ከእርሱ ብቻ ነው።

ሁሉም ነገር አንዱ ብቸኛ ኃይል ለማጥፋት ወይም ለመጥቀም፥ ለእውነት ወይም ለስሕተት፥ ለክብር ወይም ለውርደት፥ ለደስታ ወይም ለችግር ለእያንዳንዳቸው ችሎታ ነፃ በሆነ መልኩ ያለ ጥቅም እንዲጠፉ ወይም ለጥቅም የቀጠራቸው መሣሪያዎች ናቸው። ያለምንም ጭቅጭቅ ‹እርሱ ሲፈቅድ› ‹እንደፈቀደው› ይሆናል።

እንግዲህ ‹ፍቅር› የአላህ ባሕርይ እንደሆነ በቁርዓን አልተገለጸም ማለቱ እንኳን ትክክል ሊሆን አይችልም። የሁሉንም መጣሌዎች አጠቃላይ ግምገማ ስንመለከት ይህ ባሕርይ እንዳለው ያሳዩናል። እስቲ በመጀመሪያው በአሉታ የተጠቀሱትን እንመልከት፡-



አላህ የማይወዳቸው፡- ተላላፊዎችን (ሱረቱ 2፡190)

ማታለልንና አታላዮችን (ሱረቱ 2:205; 28:77; 5:67)

አራጣ አበዳሪዎችን፤ (ሱረቱ 2፡275፥ 276)

ከዳተኞችን (ሱረቱ 8፡58)

አባካኞችን (ሱረቱ 6፡141)፤ 7፡31፤ 5፡90 (ያለ ልክ በቅንጦት የሚኖሩትን)

ከገደቡ በማለፍ የሚተላለፉትን (ሱረቱ 7፡55)

ስሕተት የሚሠሩትን (ሱረቱ 3፡140፤ 42፡40)

ኩራተኞችንና ትዕቢተኞችን (ሱረቱ 4፡36፤ 16፡23)

በኩራት የሚመኩትን (ሱረቱ 31፡18፤ 57፡23)

በሐብታቸው ምክንያት በደስታ የሚሰክሩትን፥ (ሱረቱ 28፡76)

እምነትን የማይቀበሉትን፥ (ሱረቱ 30፡45)

ውለታ ቢስንና ከዳተኛን፥ (ሱረቱ 22፡38)

እምነት በማጉደልና በወንጀል (በማታለል) የተያዙትን (ሱረቱ 4፡107) ነው።

አላህ የሚወደው፡- መልካም የሚሠሩትን፥ (ሱረቱ 2፡195፤ 3፡134)

ዘወትር ወደ እርሱ የሚመለሱትንና ራሳቸውን ንጹህና ቅዱስ አድርገው የሚጠብቁትን፥ (ሱረቱ 2:222; 8:108)

የጽድቅን ሥራዎች የሚያደርጉና የሚያምኑትን፥ (ሱረቱ 19፡96)

እርሱን የሚወዱትን (ሱረቱ 3፡31)

ለእርሱ ጉዳይ በጦርነት የሚዋጉትን (ሱረቱ 61፡4)

ቅኖችን (ሱረቱ 49፡9፤ 60፡8፤ 5፡45)

ጻድቃንን (ሱረቱ 9፡4-7) ነው።

ይህ ከሁለት ጥቅሶች በስተቀር ሙሉ የሆነ ዝርዝር ነው፤ ሁለቱ ጥቅሶች፡-

«እርሱ ይቅርታው የበዛ፥ ፍቅርና-ርኅራኄን የተሞላ ነው» (ሱረቱ 85፡14)

እና

«ጌታዬ በእርግጥ ምህረትና ፍቅርን የተሞላ ሩህሩህ ነው» (ሱረቱ 11፡41)

የሚለው ነው።

የተጠቀሱት ጥቅሶች አላህ ለማን የፍቅር ርኅራኄው ብዙ እንደሆነ ይገልጻሉ፥

አላህ የሚወዳቸው ንጹህ፥ ሩኅሩኅ፥ ቅንና ጻድቅ አማኞች፥ በጎ የሚሠሩ፥ አላህን የሚወዱ፥ (ቢያስፈልግ) ለእርሱ በጦርነት የሚዋጉለት፥ የማይበድሉ ወይም በሀብት ያለ ልክ እየፈነጠዙ የማይኖሩ ወይም የማያታልሉ፥ (የእግዚአብሔርን ሕግ) የማይተላለፉ ወይም የማይጣሉ፥ በማባከን በቅንጦት የማይኖሩ፥ የሚያመሰግኑ ወይም ከፋዎች ያልሆኑ፥ ኩራተኞች ወይም በትዕቢት የማይመኩ፥ ጓደኛቸውን የማይከዱና ስሕተት የማይሠሩ ናቸው። ማነው እነዚህን ሁሉ የሚያሟላ?

ስለዚህ የአላህ ፍቅር በሁኔታዎች ላይ የተመሠረተ ነው፤ ከእግዚአብሔር አብና ከጌታችን ከኢየሱስ ፍቅር ጋር አይመሳሰልም።

«ገና ደካሞች ሳለን ክርስቶስ ዘመኑ ሲደርስ ስለ ኃጢአተኞች ሞቶአልና።»

«ነገር ግን ኃጢአተኞች ሳለን ክርስቶስ ስለእኛ ሞቷልና!» (ሮሜ 5:6 ና 8)

«ፍቅርም እንደዚህ ነው፤ እግዚአብሔር እርሱ ራሱ እንደወደደን ስለ ኃጢአታችንም ማስተሰሪያ ይሆን ዘንድ ልጁን እንደላከ እንጂ እኛ እግዚአብሔርን እንደወደድነው አይደለም። እርሱ አስቀድሞ ወዶናልና እኛ እንወደዋለን» (1 ዮሐ. 4:10፥16)።

«በወደደኝና ስለ እኔ ራሱን በሰጠው በእግዚአብሔር ልጅ ላይ ባለ እምነት የምኖረው ነው» (ገላ. 2:20)።

«... ከእግዚአብሔር ፍቅር ሊለየን እንዳይችል ተረድቼአለሁ» (ሮሜ 8:35-39)።

በሌላ በኩል ደግሞ:- መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔርን ሥልጣንና ኃይሉን አይገልጽም ማለት ስሕተት ነው።

«እነሆ እግዚአብሔር በኃይሉ ከፍ ያለውን ነገር ያደርጋል! እንደ እርሱስ ያለ አስተማሪ ማነው?» (ኢዮብ 36:22)።

«ልባቸውን የቆሰሉትን ይፈውሳል፤ ሕመማቸውንም ይጠግናል። የከዋክብትንም ብዛት ይቆጥራል፤ ሁሉንም በየስማቸው ይጠራቸዋል። ጌታችን ታላቅ ነው፤ ኃይሉም ታላቅ ነው፤ ለጥበቡም ቁጥር የለውም» (መዝ. 147:3-5)።

«አቤቱ እንደ አንተ ያለ የለም፤ አንተ ታላቅ ነህ፤ ስምህም በኃይል ታላቅ ነው። የአሕዛብ ንጉሥ ሆይ በአሕዛብ ጥበበኞች ሁሉ መካከል በመንግሥታቸውም



ሁሉ እንደ አንተ ያለ ስለ ሌለ አንተን መፍራት ይገባልና አንተን የማይፈራ ማነው?» (ኤር. 10:6-7)።

«ዓለሙን በጥበቡ የመሠረተ ሰማያትንም በማስተዋሉ የዘረጋ እርሱ ነው» (ኤር. 10:11-12)።

«ኑ፥ የእግዚአብሔርንም ሥራ እዩ፤

ከሰው ልጆች ይልቅ በምክር ግሩም ነው። ባሕርን የብስ አደረጋት፥ ወንዙንም በእግር ተሻገሩ፤ በዚያ በእርሱ ደስ ይለናል። በኃይሉ ለዘላለም ይገዛል፤ ዓይኖቹ ወደ አሕዛብ የመለከታሉ፤ ዓመፀኞች ራሳቸውን ከፍ ከፍ አያድርጉ» (መዝ. 66:5-7)።

## እግዚአብሔር ለጥቅማችን ሲል ከመለኮታዊ ባሕሪይው ተካፋይች አድርጎናል።

«የመለኮቱ ኃይል፥ በገዛ ክብሩና በበጎነቱ የጠራንን በማወቅ፥ ለሕይወትና እግዚአብሔርን ለመምሰል የሚሆነውን ነገር ሁሉ ስለሰጠን በእግዚአብሔርና በጌታችን በኢየሱስ ዕውቀት ጸጋና ሰላም ይብዛላችሁ። ስለ ክፉው ምኞት በዓለም ካለው ጥፋት አምልጣችሁ ከመለኮት ባሕሪይ ተካፋዮች በተስፋ ቃል እንድትሆኑ፥ በእነዚያ በጎነት የተከበረና እጅግ ታላቅ የሆነ ተስፋን ሰጠን» (2 ጴጥ. 1:3-4)።

«እግዚአብሔር የኃይልና የፍቅር፥ ራስንም የመግዛት መንፈስ እንጂ የፍርሃት መንፈስ አልሰጠንምና» (2 ጢሞ. 1:7)።

> እግዚአብሔር በግብሩ ማለፊያ ነው መለወጥም አይታይበትም። እርሱ ራሱም ሆነ ቃሉ አይለወጥም።
> **እርሱ ራሱን ከቃሉ ኋላ ይቆማል። ስለዚህ ሙሉ በሙሉ ልናምነው እንችላለን።**

«እኔ እግዚአብሔር አልለወጥም!» (ሚል. 3:6)።

«በጎ ስጦታ ሁሉ፥ ፍጹምም በረከት ሁሉ ከላይ ናቸው፤ መለወጥ በርሱ ዘንድ ከሌለ በመዞርም የተደረገ ጥላ በርሱ ዘንድ ከሌለ ከብርሃናት አባት ይወርዳሉ» (ያዕ. 1:17)።

«ስለዚህ እግዚአብሔር የተስፋውን ቃል ለሚወርሱ ፈቃዱ እንደማይለወጥ አብልጦ ሊያሳያቸው ስለፈቀደ እግዚአብሔር ሊዋሽ በማይቻል በሁለት

በማይለወጥ ነገር፥ በፊታችን ያለውን ተስፋ ለመያዝ ለሸሸን ለእኛ ብርቱ መጽናናት ይሆንልን ዘንድ በመሐላ በመካከል ገባ፤ ይህም ተስፋ እንደ ነፍስ መልሕቅ አለን፤ እርሱም እርግጥና ጽኑ የሆነ ወደ መጋረጃው ውስጥ የገባ ነው» (ዕብ. 6:17-19)።

በመጨረሻም እግዚአብሔር የክፋትና የኃጢአት ምንጭ እንዳልሆነ፥ እንዲሁም ፈቃዱ እንዳልሆነ ለመግለጽ እንወዳለን። እግዚአብሔር ከቁጣ የራቀ ነው። እንዲሁም ዐዘንንና መከራን ሰዎችን ወደ እምነትና ወደ መልካምነት ለመጥራት ይጠቀምበታል።

አላህ:- በአላህ በኩል ይህ ሊባል የማይቻል ነገር ነው። እርሱ ደስ እንዳለው ነው የሚያደርገው:-

ሱረቱ 14:4 « ከመልእክተኛ ማንኛውንም ለነርሱ
ያብራራላቸው ዘንድ በወገናቹ
ቋንቋ እንጂ በሌላ አልላክንም፤
አላህም የሚሻውን ያጠምማል፤
የሚሻውንም ያቀናል። እርሱም
አሸናፊው ጥበበኛ ነው።»

ሱረቱ 16:93:- «አላህም ባሻ ኖሮ አንድ ሕዝብ
ባደረጋችሁ ነበር፤ ግን የሚሻውን
ሰው ያጠምማል፤ ሻውንም ሰው
ያቀናል፤ ትሠሩት
ከነበራችሁትም ሁሉ በእርግጥ
ትጠየቃላችሁ።»

ሱረቱ 32:13:- «በሻንም ኖር ነፍስን ሁሉ
ቅንነቷን (እምነቷን) በሰጠናት
ነበር፤ ግን «ገሃነምን ከአጋንንትና
ከሰዎች የተሰበሰቡ ሆነው
በእርግጥ እምላለሁ» ማለት ቃሉ
ከኔ ተረጋግጧል።

በተጨማሪም ሱረቱ 37:96፤ 76:29-30፤ 4:88፤ 16:36፤ 6:149፤ 7:158ን አንብብ።

በተጨማሪም ደግሞ ሌላ በጣም በጉልህ የሚታይ የሐሳብ ግጭት አለ:- የመሻር ሕግ።

ሱረቱ 17:86. ብንሻም ያንን ወዳንተ ያወረድነውን
በእርግጥ እናስወግዳለን፤ ከዚያም



ላንተ በኛ ላይ በርሱ (ለማስመለስ) ተያዥን አታገኝም።

በእርግጥ አላህ ውስዱል፤ ነገር ግን ይህ በማሻሻል ረገድ እንደሆነ ተገልጾልናል:-

ሱረቱ 2:106:- ከአንቀጽ ብንለውጥ ወይም
እርሷን ብናስረሳህ ከርሷ
የሚበልጥን ወይም ብጤዋን
እናመጣለን፤ አላህ በነገሩ ሁሉ
ላይ መሆኑን አታውቅምን?

ሱረቱ 16:101:- በአንቀጽም ስፍራ አንቀጽን
በለወጥን ጊዜ፥ አላህም
የሚያወርደውን ነገር አዋቂ
ነው፤ «አንተ ቀጣፊ እንጂ
ሌላ አይደለህም» ይላሉ፤
በእውነቱ አብዛኞቻቸው
አያውቁም።

የሚጋጩትንና የሚቃረኑትን ዓረፍተ ነገሮች ስንመለከት፥ መሐመድ እያስመሠለና እየቀየረ የሚጽፍ ነው የሚሉትን ሰዎች ለመቃወም በጣም ያስቸግራል:-

ሱረቱ 6:34:- የአላህንም ንግግሮች ለዋጭ የለም፤ ከመልእክተኞቹም ወሬ
(የምትረጋጋበት) በእርግጥ መጣልህ።

ሱረቱ 10:64 የአላህ ቃላት መለወጥ የላትም፤ ይህ እርሱ ታላቅ ዕድል ነው።

ይህ ታላቅ ዕድል እያሰብን የላይኞቹን ጥቅሶችና የመጨረሻዎቹን ሁለቱን ተቃራኒ ጥቅሶች ስንመለከት በቅጽበት በመትነን ወደ ሐዘን ይለወጣል። በእርግጥ በከፍተኛ መጠንና ደረጃ ‹የተገለጡ› ቃሎች መሻራቸውንና አብዛኞቹ በሌላ መተካታቸውን እናውቃለን። («እስልምና ስለ ራሱ ያለው አመለካከት ሌሎች ያላቸው አመለካከትና ምንነቱ» ገጽ 75-78 ተመልከት)።

## ማጠቃለያ

ስለ አላህና ስለ ‹እግዚአብሔር› ተፈጥሮና ባሕርይ እንዲሁም ስለ መሲሑ ኢየሱስ የተገለጸው የቁርዓንና የመጽሐፍ ቅዱስ ተቃራኒ ትምህርቶች ሊታረቁ የማይችሉ ናቸው። ከዚህ የምንገነዘበው የሁለቱ መጻሕፍት መገለጦች ከሁለት የተለያዩ ምንጮች እንደተገኙ ሲሆን፥ አላህና እግዚአብሔር የአንድ አምላክ የተለያዩ ስሞች ናቸው ብሎ ለመገመት በጣም ያስቸግራል።

## የሰው ተፈጥሮ በቁርዓንና በመጽሐፍ ቅዱስ አመለካከት

ከሁለቱም መጻሕፍት በዚህ ጉዳይ ላይ ጠቃሚ የሆኑ ጥቅሶችን ስንመለከት የሚመሳሰሉበትንና የሚለያዩበትን ቦታ መገንዘብ እንችላለን። እስቲ እንመልከታቸው:-

### መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ሰው ድርሻና ቦታ ያለው አመለካከት

እግዚአብሔር ሰውን ፈጠረ:-

«እግዚአብሔርም አለ፥ ሰውን በመልካችን እንደ ምሳሌያችን እንፍጠር፥ የባሕር ዓሦችንና የሰማይ ወፎችን፥ እንስሳትንና ምድርን ሁሉ፥ በምድር ላይ የሚንቀሳቀሱትን ሁሉ ይግዙ። እግዚአብሔርም ሰውን በመልኩ ፈጠረ፤ በእግዝኢአብሔር መልክ ፈጠረው ወንድና ሴት አድርጎ ፈጠራቸው» (ዘፍ. 1:26-27)።

«እግዚአብሔርም ያደረገውን ሁሉ አየ እነሆም እጅግ መልካም ነበር። ማታም ሆነ ጠዋትም ሆነ ስድስተኛ ቀን» (ዘፍ. 1:31)።

«እግዚአብሔር አምላክም ሰውን እንዲህ ብሎ አዘዘው:- ›ከገነት ዛፍ ሁሉ ትበላለህ ነገር ግን መልካምና ክፉን ከሚያስታውቀው ዛፍ አትብላ፥ ከእርሱ በበላህ ቀን ሞትን ትሞታለህና» (ዘፍ. 2:15-17)።

አዳም የተሰጠውን የምርጫ ነፃነት ያለ አግባብ ስለተጠቀመበት ሞትን አስከተለ:-

«ለሴቲቱም አለ:- ›በፀነስሽ ጊዜ ጭንቅሽን እጅግ አበዛዋለሁ፤ በጭንቅ ትወልጃለሽ፤ ፈቃድሽም ወደ ባልሽ ይሆናል እርሱም ገዥሽ ይሆናል።› አዳምንም አለው:- የሚስትህን ቃል ሰምተሃልና፥ ከእርሱ እንዳትበላ ካዘዝኩህ ዛፍም በልተሃልና፥ ምድር ካንተ የተነሣ የተረገመች ትሁን፤ በሕይወት ዘመንህም ሁሉ በድካም ከእርሷ ትበላለህ፤ እሾህንና አሜከላን ታበቅልብሃለች፤ የምድርንም ቡቃያ ትበላለህ። ወደ ወጣህበት መሬት እስክትመለስ ድረስ በፊትህ ወዝ እንጀራን ትበላለህ፤ አፈር ነህና ወደ አፈርም ትመለሳለህና» (ዘፍ. 3:16-19)።

የሰው ኃጢአተኛ ባሕርይ እግዚአብሔርን ያሳዝነዋል:-

«እግዚአብሔርም የሰው ክፋት በምድር ላይ እንደበዛ የልቡ አሳብ ምኞትም ሁልጊዜ ፈጽሞ ክፉ እንደሆነ አየ። እግዚአብሔርም ሰውን በምድር ላይ በመፍጠሩ ተጸጸተ፤ በልቡም አዘነ» (ዘፍ 6:5-6)።



«የሰውም ልብ ከሁሉ ይልቅ ተንኮለኛ እጅግም ክፉ ነው፤ ማንስ ያውቀዋል? እኔ እግዚአብሔር ለሰው ሁሉ እንደመንገዱ፥ እንደ ሥራው ፍሬ እሰጥ ዘንድ ልብን እመረምራለሁ ኩላሊትንም እፈትናለሁ» (ኤር. 17:9-10)።

ኢየሱስ መሠረታዊ ችግሩ ያለበትን ቦታ በትክክል ጠቁሟል:-

«ከውስጥ ከሰው ልብ የሚወጣ ክፉ ሐሳብ፥ ዝሙት፥ መስረቅ፥ መግደል፥ ምንዝርነት፥ መጎምጀት፥ ክፋት፥ ተንኮል፥ መዳራት፥ ምቀኝነት፥ ስድብ፥ ትዕቢት፥ ስንፍና ናቸውና ይህ ክፉው ሁሉ ከውስጥ ይወጣል ሰውንም ያረክሰዋል» (ማር. 7:21-23)።

የሰው ልብ ክፉ ስለሆነ፥ የእግዚአብሔር ፍርድ ደግሞ አስፈሪና አውዳሚ ነው:-

«እንግዲህ ምን ይሁን? ከእነርሱ እንበልጣለንን? ከቶ አይደለም፤ አይሁድም የግሪክ ሰዎችም ሁሉ ከኃጢአት በታች እንደሆኑ አስቀድመን ከሰናቸዋልና፤ እንዲህ ተብሎ እንደተጻፈ:- ጻድቅ የለም አንድ ስንኳ፤ አስተዋይም የለም፤ እግዚአብሔርንም የሚፈልግ የለም፤ ሁሉ ተሳስተዋል በአንድነትም የማይጠቅሙ ሆነዋል፤ ቸርነት የሚያደርግ የለም፥ አንድ ስንኳ የለም። ጉሮሮአቸው እንደተከፈተ መቃብር ነው፥ በመላሳቸውም ሸንግለዋል፤ የእባብ መርዝ ከከንፈሮቻቸው በታች አለ፤ አፋቸውም እርግማንና መራርነት ሞልቶበታል፤ እግሮቻቸው ደምን ለማፍሰስ ፈጣኖች ናቸው፤ ጥፋትና ጉስቁልና በመንገዳቸው ይገኛል፥ የሰላምንም መንገድ አያውቁም። በዓይኖቻቸው ፊት እግዚአብሔርን መፍራት የለም፥» (ሮሜ 3:9-18)።

ምንም እንኳ እግዚአብሔር ሰውን ከፍጥረት ሁሉ በላይ አድርጎ ኃላፊነትን ቢሰጠውም የሚከተለው እውነት የሚታበል አይደለም:-

«ታስበው ዘንድ ሰው ምንድነው? ትጎበኘውም ዘንድ የሰው ልጅ ምንድነው? ከመላእክት እጅግ ጥቂት አሳነስከው፤ በክብርና በምስጋና ዘውድ ከለልከው። በእጆችህም ሥራ ሁሉ ላይ ሾምከው፤ ሁሉን ከእግሮቹ በታች አስገዛህለት፥ በጎችንም ላሞችንም ሁሉ፥ ደግሞም የምድረበዳውን እንስሶች፥ የሰማይ ወፎች የባሕርንም ዓሦች፥ በባሕር መንገድ የሚሄደውን ሁሉ» (መዝ. 8:4-8)።

የሰው ባሕርይ እንዲህ ቢሆንም፥ እግዚአብሔር አልተወውም። በተቃራኒው:-

«እግዚአብሔር፥ እግዚአብሔር መሐሪ፥ ሞገስ ያለው፥ ታጋሽም፥ ባለብዙ ቸርነትና እውነት፥ እስከ ሺህ ትውልድም ቸርነትን የሚጠብቅ፥ አበሳንና መተላለፍን ኃጢአትንም ይቅር የሚል፥ በደለኛውንም ከቶ የማያነፃ» (ዘፀ. 34፡6፤ መዝ. 103፡8-14)።

«እግዚአብሔርም ከሩቅ ተገለጠልኝ እንዲህም አለኝ፡- በዘላለም ፍቅር ወድጄሻለሁ ስለዚህ በቸርነት ሳብሁሽ» (ኤር. 31፡3)።

የእግዚአብሔር ፍቅር እኛ የበደላችንን ቅጣት በእኛ ፋንታ እርሱ ራሱ እንዲሸከም አደረገው፡-

«ገና ደካሞች ሳለን ክርስቶስ ዘመኑ ሲደርስ ስለ ኃጢአተኞች ሞቷልና። ስለ ፃድቅ የሚሞት በጭንቅ ይገኛልና፤ ስለ ቸር ሰው ግን ሊሞት እንኳ የሚደፍር ምናልባት ይገኝ ይሆናል። ነገር ግን ገና ኃጢአተኞች ሳለን ክርስቶስ ስለ እኛ ሞቷልና እግዚአብሔር ለእኛ ያለውን የራሱን ፍቅር ያስረዳል። ይልቁንስ እንግዲህ አሁን በደሙ ከጸደቅን በእርሱ ከቁጣው እንድናለን» (ሮሜ 5፡6-9)።

እግዚአብሔር ሰውን ይወዳል። ሰው ንስሐ እንዲገባና የእግዚአብሔርን መሥዋዕት እንዲቀበል፥ እንዲሁም እሱን እያከበረው በእርሱ እንዲሞላ ይፈልጋል፡-

«... ከአብ ፊት እንበረከካለሁ፤ በመንፈሱ በውስጥ ሰውነታችሁ በኃይል እንድትጠነክሩ ክርስቶስም በልባችሁ በእምነት እንዲኖር እንደ ክብሩ ባለጠግነት መጠን ይስጣችሁ፤ የእናንተ ሥርና መሠረት በፍቅር ይጸና ዘንድ፥ ከቅዱሳን ሁሉ ጋር ስፋቱና ርዝመቱ ከፍታውም ጥልቅነቱም ምን ያህል መሆኑን ለማስተዋል፥ ከመታወቅም የሚያልፈውን የክርስቶስን ፍቅር ለማወቅ ትበረቱ ዘንድ፥ እስከ እግዚአብሔርም ፍጹም ሙላት ደርሳችሁ ትሞሉ ዘንድ» (ኤፌ. 3፡17-19)።

እርሱ የሰጠን ከይቅርታና ከፍቅር የላቀ ነገር አለ፡- ይኸውም ከመለኮታዊ ባሕሪውን ሰጥቶናል።

«የመለኮቱ ኃይል በገዛ ክብሩና በበጎነቱ የጠራንን በማወቅ ለሕይወትና እግዚአብሔርን ለመምሰል የሚሆነውን ነገር ሁሉ ስለሰጠን፥ በእግዚአብሔርና በጌታችን በኢየሱስ እውቀት ጸጋና ሰላም ይብዛላችሁ። ስለ ክፉ ምኞት በዓለም ካለው ጥፋት አምልጣችሁ ከመለኮት ባሕርይ ተካፋዮች በተስፋ ቃል እንድትሆኑ በእነዚያ ክብርና በጎነት የተከበረና እጅግ ታላቅ የሆነ ተስፋን ሰጠን» (2 ጴጥ 1፡3-4)።



በኢየሱስ ክርስቶስ የተዋጁት ከእግዚአብሔር ደግሞ የተወለዱት እነርሱ - የእግዚአብሔር ልጆች የሆኑ ናቸው፡-

«... እኔ ሕይወት እንዲሆንላቸው እንዲበዛላቸውም መጣሁ» (ዮሐ 10፡10)።

«ለተቀበሉት ሁሉ ግን፥ በስሙ ለሚያምኑት ለእነርሱ የእግዚአብሔር ልጆች ይሆኑ ዘንድ ሥልጣንን ሰጣቸው፤ እነርሱም ከእግዚአብሔር ተወለዱ እንጂ ከደም ወይም ከሥጋ ፈቃድ ወይም ከወንድ ፈቃድ አልተወለዱም» (ዮሐ. 1፡12-13)።

## ቁርዓን ስለ ሰው ድርሻና ቦታ ያለው አመለካከት

አላህ ሰውን ፈጠረ፡-

ሱረቱ 32፡7 ያ የፈጠረውን ነገር ሁሉ
ያሳመረው፥ የሰውንም
ፍጥረት ከጭቃ
የጀመረው ነው።

8፡ ከዚያም ዘሮቹን ከተጣለለ ከደካማ
ውኃ ያደረገ ነው።

9፡ ከዚያም (ቅርጹን) አስተካከለው፤
በርሱ ውስጥም ከመንፈሱ
ነፋበት፤ (ነፍስ ዘራበት)፤
ለእናንተም ጆሮችን፥ ዐይኖችንና፥
ልቦችንም አደረገላችሁ፤ በጣም
ጥቂትን ብቻ ታመሰግናላችሁ።

ሱረቱ 96፡-2. ሰውን ከረጋ ደም
በፈጠረው፡-

(በተጨማሪ ሱረቱ 6፡2፤ 23፡12-14፤
75፡36-39፤ 95፡4-5 ን ተመልከት)።

ሰው የተፈጠረበት ዓላማና ተፈጥሯዊ
ባሕሪይ፡-

ሱረቱ 51፡-56. ጋኔንና ሰውንም ሊገዙኝ
እንጂ ለሌላ
አልፈጠርኳቸውም።

ሱረቱ 90፡-4. ሰውን ሁሉ በእርግጥ
በልፋት ውስጥ ሆኖ
ፈጠርነው።

ሱረቱ 4፡-28. አላህ ችግራችሁን
ሊያቃልልላችሁ ይሻል።
ሰውም ደካማ ሆኖ
ተፈጠረ።

ሱረቱ 50፡-16. ሰውንም ነፍሱ (በሐሳቡ)
የምታጫውተውን
የምናውቅ ስንሆን፥
በእርግጥ ፈጠርነው፤
እኛም ከደም ጋኑ ጅማት
ይበልጥ ወደርሱ ቅርብ
ነን።

ሱረቱ 70፡-19. ሰው ቅጠቢስ ሆኖ ተፈጠረ።
20. ክፉ ነገር ባገኘው ጊዜ ብስጪተኛ፥
21. መልካም ነገር (ድሎት) ባገኘ ጊዜ
ከልካይ (ሆኖ ተፈጠረ)።

ሱረቱ 17፡100 ሰውም በጣም ቆጣቢ ነው።

ሱረቱ 17፡67 ሰውም በጣም ከሐዲ ነው።

ሱረቱ 18፡-7. እኛ ማንኛቸው ሥራው
ያማረ መሆኑን
ልንፈትናቸው በምድር
ላይ ያለን ሁሉ ለርሷ ጌጥ
አደረግን።

ሱረቱ 14፡-34. ከለመናችሁትም ሁሉ
የሰጣችሁ ነው፤

የአላህንም ጸጋ ብትቆጥሩ አትዘልቋትም፤

ሰው በጣም በደለኛ ከሐዲ ነው።

ሱረቱ 17፡-83. በሰውም ላይ ጸጋችንን
በለበስን ጊዜ፥ (ከምስጋና)
ይዞራል፤ ጎኑንም



(ከእውነት) ያርቃል፤ ችግርም
በነካው ጊዜ ተስፋ ቆራጭ
ይሆናል።

ሱረቱ 100፡-6. ሰው ለጌታው ብርቱ ከሐዲ ነው።
7. እርሱም በዚህ ላይ መስካሪ ነው።
8. እርሱም ገንዘብን ለመውደድ በጣም ብርቱ
ነው።

ሰውን የሚቀጣና የሚሸልም አላህ፡-

ሱረቱ 33፡-73. መናፍቃንን መናፍቃትን፥
ወንዶች አጋሪዎችንና ሴቶች
አጋሪዎችንም፥ አላህ ሊቀጣና
በምእመናንና በምእመናትም ላይ
አላህ ንስሐን ሊቀበል (አደራዋን
ሰው ተሸከማት)፤ አላህም
መሐሪ አዛኝ ነው።

ሱረቱ 13፡-6. ከነሱ በፊት የመሰሎቻቸው
ቅጣቶች በእርግጥ ያለፉ ሲሆኑ፥
ከመልካሙ በፊት በመጥፎው
ያስቸኩሉሃል፤ ጌታህም ለሰዎች
ከመበደላቸው ጋር በእርግጥ
የምሕረት ባለቤት ነው፤ ጌታህም በእርግጥ ቅጣቱ ብርቱ ነው።

አስተውሎ የሚያነብ ሰው የሚመሳሰልበትንና መሠረታዊ ልዩነቱን ሊገነዘብ ይችላል። በተጨማሪም የአላህና ‹እግዚአብሔር› ፅንሰ ሐሳብ የተለያየ መሆኑን በድጋሚ መመልከት ይችላል።

እስቲ በሁለቱ መጻሕፍት ያለውን ተመሳሳይነት እንመልከት፡-

ሰው የእግዚአብሔር ፍጡር ነው።

ሰው ደካማ፥ ኃጢአተኛና የሥነ-ምግባር ጉድለት ያለበት ነው።

የማያምኑና (ግብዞች) ይቀጣሉ፤ እንዲሁም አማኞች ይቅርታን ያገኛሉ፤ ብድራታቸውንም ይቀበላሉ።

ከዚህ የምናስተውለው፡-

የሰው አፈጣጠር (ከሸክላ:- ሱረቱ 6:22፤ 32:7፤ ከረጋ ደም ሱረቱ 96:2፤ ከወንድ ዘር:- ሱረቱ 23:12-13፤ 80:18-19)፡

የተፈጠረበት ዓላማ (አላህን ለማገልገል:- ሱረቱ 51:56፤ እንዲለፋና እንዲደክም:- ሱረቱ 90:4፤ እንደሚያንፀባርቅ ጌጥ እንዲታይ:- ሱረቱ 18:7)።

የአፈጣጠሩ ጥራት (ሰው ደካማ ተደርጎ ነው የተፈጠረው:- ሱረቱ 4:28፤ በነፍሱ ውስጥ ከክፉ አስተሳሰብ ጋር:- ሱረቱ 50:16፤ የማይታገስ:- ሱረቱ 70:19፤ በክፉ ነገር የሚበሳጭ:- ሱረቱ 70:20፤ ገብጋባ:- ሱረቱ 70:21፤ 17:100፤ የማያመሰግን:- ሱረቱ 100:6-8፤ ለፍትሕ መጓደልና ለምስጋናቢስነት የተሰጠ:- ሱረቱ 14:34፤ አደገኛ የገንዘብ ፍቅር ያለው:- ሱረቱ 100:8)።

ከላይ የተጠቀሱትን ነጥቦች በጥልቀት ማጥናት ጠቃሚታ አለው።

ስለ ሰው ድርሻና ቦታ ያለው የተለያየ አመለካከት የተመሠረተበት ነገር ቀጥሎ ያለው ነው

## ቁርዓንና መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ኃጢአት ያላቸው አመለካከት

በመጀመሪያ ስለ እግዚአብሔር ያላቸውን አንዳንድ መሠረታዊ የሆኑ የጽንሰ-ሐሳብ ልዩነቶችን ማስተዋል አለብን:-

**መጽሐፍ ቅዱስ:-**

‹እግዚአብሔር› በመጀመሪያ ከፈጠረ በኋላ ሰዎችን ለራሱ መረጠ። አስቀድሞ ግለሰቦችን፥ ከዚያም የእሥራኤልን ሕዝብ መረጠ። በአዲስ ኪዳን ደግሞ በእውነት የሚፈልጉትን፥ መሥዋዕት ሆኖ የቀረበውን አዳኝ ኢየሱስ ክርስቶስን እንደ ጌታ የተቀበሉትንና ለፍቅሩም በጎ ምላሽ የሚሰጡትን ይመርጣል።

እግዚአብሔር ሰይጣንን፥ ክፋትን፥ ወይም ኃጢአትን አልፈጠረም። እነዚህ ሁሉ የመጡት እግዚአብሔር ለሰዎችና ለመላእክት ከሰጠው የምርጫ ነፃነት ሲሆን፥ ይህም እግዚአብሔርን በእውነት ፈቅደን እንድንወደው የሚያስችለን ነገር ነው። እግዚአብሔር ፍጹምነትና ኃጢአት -አልባነትን ከእኛ ይጠብቃል፤ ምክንያቱም እርሱ ቅዱስ ስለሆነ ከ ኃጢአተኛ ሰው ጋር ኅብረት ሊኖረው አይችልም።

ከዚህ የተነሣ እግዚአብሔር ለሰው የሌለውን ነገር ማለትም የርሱን ጽድቅ፥ ይቅርታ፥ፍቅር፥ቅድስና ሰጥቶታል። እግዚአብሔር ፍቅር ስለሆነ፥ ማንም እንዲጠፋ አይፈልግም። ቢሆንም ቅሉ እግዚአብሔርየሰው የምርጫ ነፃነት ስለሚያከብር፥ ማንም የወደደውን ለማገልገል መመረጥ ይችላል። የእግዚአብሔር መንግሥት ደግሞ እግዚአብሔር ባለበት ቦታ መሆን አለበት። እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ኅብረት ማድረግ ይፈልጋል።

**እስልምና:-**

አላህ አለምን በሙሉ ይገዛል፤እንዲሁም በምድር ያሉ ሰዎች ሁሉ እንዲገዙለት ያዛል። የአላህ ፈቃድ የሰዎችን ፀባይና ድርጊታቸውን ሁሉ ምን መሆን እንዳለበት በሚያዘው ጤሪያ ሕግ አማካኝነት በሚቻልበት ቦታ ሁሉ ይህ ተ ደንግጎ መከበር አለበት። የዚህም ዓላማ የአላህን ሕግ በሁሉ ቦታ ተፈጻሚነት እንዲኖረው ለማስገደድ ነው።

አላህ ታላቅ ነው። ስለዚህ ደስ ያሰኘውን ይቅር ሊል ይችላል። ሁሉም ኃጢአተኞች ጻድቃን ቢሆኑ እሱ ምንም ጥቅም አያገኝም፤እንዲሁም ሁሉም አማኞች ከሐዲ ቢሆኑ ምንም አይጎዳም። አላህ የኃጢአትም ፈጣሪ ነው። አንዳንዶች ኃጢአት እንዲያደርጉ ይፈቅዳል፤ አንዳንዶች ደግሞ ለእርሱ ታዛዥና ሃይማኖተኛ እንዲሆኑ ይፈቅዳል። ይቅርታን የሚያደርገው ኃጢአትን በራሱ ዋጋ (መሥዋዕትነት)በማስወገድ ሳይሆን፥ እንዲሁ በፈቃዱ ነው። ገነት የትክክለኛ ሥነ-ምግባር ሽልማት ወይም ከአላህ በድንገት በዕድል የሚገኝ የይቅርታ ውጤት ነው። ገነት የሰው ፍላጎትና ምኞት ፍፃሜ ናት።

ኃጢአት በእግዚአብሔር ቅድስናና ጽድቅ ላይ የሚሠራ ከባድ ወንጀል ነው፤ ምክንያቱም ኃጢአት በእግዚአብሔር ላይ ማመፅ ወይም ለእግዚአብሔር ግድ የለሽ መሆን ማለት ነው። ሰው በራሱ ኃጢአትን በመሥራቱ ይደሰታል። ኃጢአትን የሚጠላና በኃጢአቱም የሚያዝን የእግዚአብሔር መንፈስ የሚኖርበትና የሚሠራበት ሰው ብቻ ነው። (ይህም ኃጢአት መሥራቱ ሲታወቅበት ብቻ አይደለም!)

**በመሠረቱ መጽሐፍ ቅዱስ ሰይጣን የኃጢአት ምንጭ መሆኑን እንደሚያስተምር መገንዘብ አለብን። በአንፃሩ ደግሞ እስልምና:- አላህ ኃጢአትን ጨምሮ የሁሉ ነገር ምንጭ ነው ይላል።**

## መጽሐፍ ቅዱስ

«አዳምና ሚስቱ ሁለቱም ዕራቁታቸውን ነበሩ፤ አይተፋፈሩም ነበር። እባብም እግዚአብሔር አምላክ ከፈጠረው ከምድር አውሬ ሁሉ ይልቅ ተንኰለኛ ነበር። ሴቲቱንም:- በውኑ እግዚአብሔር ከገነት ዛፍ ሁሉ እንዳትበሉ አዝዞአልን? አላት። ሴቲቱም ለእባቡ አለችው:- በገነት ካለው ከዛፍ ፍሬ እንበላለን ነገር ግን በገነት መካከል ካለው ከዛፍ ፍሬ፥ እግዚአብሔር አለ:- እንዳትሞቱ ከእርሱ አትብሉ አትንኩትም። እባብም ለሴቲቱ አላት:- ሞትን አትሞቱም፤ ከእርስዋ በበላችሁ ቀን ዓይኖቻችሁ እንዲከፈቱ እንደ እግዚአብሔርም መልካምንና ክፉን የምታውቁ እንድትሆኑ እግዚአብሔር ስለሚያውቅ ነው እንጂ። ሴቲቱም ዛፍ ለመብላት ያማረ እንደሆነ፥ ለዓይንም እንደሚያስጎመጅ፥ በጥበብም መልካም እንደሆነ አየች፤ ከፍሬውም ወሰደችና በላች፤ ለባልዋም ደግሞ ሰጠችው፤ እርሱም ከእርሷ ጋር በላ። የሁለቱም ዓይኖች ተከፈቱ፥ እነርሱም እራቁታቸውን እንደሆኑ አወቁ፤ የበለስንም ቅጠሎች ሰፍተው ለእነርሱ ለራሳቸው ግልድም አደረጉ» (ዘፍ. 2:25-3:7)።

«እግዚአብሔርም ሰዎችን ቅኖች አድርጎ እንደሠራቸው፥ እነሆ ይህን ብቻ አገኘሁ፤ እነርሱ ግን ብዙ ብልሃትን ፈለጉ» (መክ. 7:29)።

ኢየሱስ ክርስቶስ በንግግሩ ስለ ኃጢአት ጅማሬ ይህን እውነት ግልጽ አድርጎታል:-

«ኢየሱስም አላቸው:- እግዚአብሔርስ አባታችሁ ከሆነ በወደዳችሁኝ ነበር፤ እኔ ከእግዚአብሔር ወጥቼ መጥቻለሁና፤ እርሱ ላከኝ እንጂ ከራሴ አልመጣሁምና። ንግግሬን የማታስተውሉ ስለምንድር ነው? ቃሌን ልትሰሙ ስለማትችሉ ነው። እናንተ ከአባታችሁ ከዲያቢሎስ ናችሁ፥ የአባታችሁንም ምኞት ልታደርጉ ትወዳላችሁ። እርሱ ከመጀመሪያ ነፍስ ገዳይ ነበር፤ እውነትም በእርሱ ስለሌለ በእውነት አልቆመም። ሐሰትን ሲናገር ከራሱ ይናገራል፥ ሐሰተኛ የሐሰትም አባት ነውና» (ዮሐ. 8:42-44)።



ምንም እንኳ በሮሜ 4:15፤ 5:13 እና በ1 ዮሐ. 3:4፤ 7:7 ኃጢአት ከእግዚአብሔር ሕግ ጋር የተያያዘ ነገር እንዳለው፥ ቢያሳይም ይህም ማለት ግን ሕጉ ኃጢአት ምን እንደሆነ ለማመልከት ሲባል ነው። ባጠቃላይ የእግዚአብሔር ባሕርይና ቅድስናው የሕግ መሠረት ነው:-

«እግዚአብሔርም ሙሴን እንዲህ ብሎ ተናገረው:- ›ለእስራኤል ልጆች ማኅበር ሁሉ እንዲህ በላቸው:- እኔ እግዚአብሔር አምላካችሁ ቅዱስ ነኝና እናንተ ቅዱሳን ሁኑ» (ዘሌ. 19:1-2)።

ነገር ግን በመጨረሻ ምርጫው የሰው ነው።

«ተመልከት፤ ዛሬ በፊትህ ሕይወትንና መልካምነትን:- ሞትንና ክፋትን አኑሬአለሁ። በፊታችሁ ሕይወትንና ሞትን በረከትንና መርገምን እንዳስቀመጥሁ እኔ ዛሬ ሰማይንና ምድርን በአንተ ላይ አስመሰክራለሁ፤ እንግዲህ...ሕይወትን ምረጥ፤ ...» (ዘዳ 30:15፥19)።

«... የምታመልኩትን ዛሬ ምረጡ፤» (ኢያ. 24:15)።

ኃጢአት መሥራት ማለት እግዚአብሔር ለእኛ ያለውን ዓላማ ማጣት ማለት ነው! ኃጢአት ከእግዚአብሔር ፈቃድ ጋር በመቃረን የሚገለጽ የሰው ፈቃድ ነው። ምንም እንኳ ሕግ ስለ ኃጢአት ለመገመት እንደመለኪያ ገመድ ቢያገለግልም፥ ኃጢአት ሕግን መተላለፍ ሳይሆን፥ ይልቁንም ለእግዚአብሔር ያለን የተበላሸ ግምት ነው። ለኃጢአት የሚገፋፋን ሁልጊዜ ሰይጣን ነው። ነገር ግን የሰይጣንን ፈተና ላለመቀበል የምርጫ ነፃነት አለን፤ በተጨማሪም ለምናደርገው ነገር ሁሉ በኃላፊነት ተጠያቂዎች ነን። አንድ ሰው ክፉን እንዲሠራ በሰይጣን ሲፈተን፥ በዚያው ፈተና እግዚአብሔርም የሰውየውን ታማኝነትና ለእርሱ ያለውን መሰጠት ይመዝንበታል።

### እስልምና:-

ሱረቱ 9:51. አላህ ለእኛ የጻፈልን
የሚጠቅም እንጂ ሌላ
አይነካንም፤ እርሱ
ረዳታችን ነው፤ በአላህ
ላይም ምእመናን ይመኩ
በላቸው።

ሱረቱ 37:95. አላቸው:-
የምትጠርቡትን
ትገዛላችሁን?

96 አላህ እናንተንም የምትሠሩትንም
የፈጠረ ሲሆን?

ሱረቱ 91:7. በነፍስም ባስተካከላትም፥
8. አመጣዋንና ፍርሃትዋን ባሳወቃት
(እምላክ፥ እምላለሁ)።

(ወይም እንዲህ ተብሎ ቢነበብ:- «እሱ (አላህ) በእስትንፋስ ቀርቦ ክፋትንና በጎነትን ባስታወቃት» (ሚሽካት 3 ገጽ 104)።

ምናልባት ሰዎች ሁሉ ሙሉ በሙሉ፥ አላህ አስቀድሞ የወሰነውን መሥራት እንዳለባቸው የሚያሳዩትን ከላይ የተጠቀሱትን ጥቅሶች የሚቃወም ይኖር ይሆናል። ነገር ግን ይህ ሐሳብ በትክክል ከቁርዓን የተገኘ ነው:-

ሱረቱ 76:29. ይህች መገሠጫ ናት፤ የሻም ሰው ወደ ጌታው መንገድን ይይዛል።
30. አላህም ካለው በስተቀር አትሹም፤ አላህ
አዋቂ ጥበበኛ ነውና።
31. የሚሻውን ሰው በእዝነቱ ውስጥ
ያስገባዋል፤ በዳዮቹንም (ዝቶባቸዋል)፤
ለነሱ አሳማሚ ቅጣትን አዘጋጅቶላቸዋል።

ከላይ በተጠቀሱት ጥቅሶች መሠረት አላህ ሰዎችን ከ «ጌታው መንገድ» (ከትክክለኛው) ለማገድ እንደሚችል ይታያል። አሁንም ቢሆን ጥፋተኛ ሆኖ ሊጠየቅ የማይችለውንም ሆነ ከባድ ቅጣት የተዘጋጀለትን ሰው የምርጫ ነፃነት አልሰጣቸውም።

አሁን እንግዲህ የ «አል-ባርቃዊ» ን ቃል ለማስታወስ እንገደዳለን:-

ምንም ነገር ይሁን እርሱ ምንም አይጠቀምም፤ ምንም አይጎዳም። ሁሉም ከሐዲዎች እንዲሁም ለክሕደታቸው በጣም ራሳቸውን የሰጡ ሃይማኖት የለሾች አማኞች ቢሆኑ እንኳ እርሱ ምንም ጥቅም አያገኝም። በሌላ በኩል ደግሞ ሁሉም አማኞች ከሐዲዎች ቢሆኑ፥ እርሱ ምንም አይጎድልበትም። የወደደውን መሥራት ይችላል፤ እርሱ የፈቀደው ሁሉ ደግሞ ይፈጸማል። አንድም ነገር እንዲያደርግ አይገደድም። በዚህ ዓለም ያለ ሁሉም፥ መጥፎም ሆነ ጥሩ ነገር ሁሉ የሚኖረው በእርሱ ፈቃድ ነው። የአማኙን እምነትና የሃይማኖተኛውን መገዛት ይፈቅዳል። ፈቃዱን ቢቀይር ኖሮ፥ ማንም እውነተኛና ራሱን የሰጠ አማኝ፥ ወይም ከሐዲ ሊኖር



አይችልም ነበር። በተጨማሪም የማያምነውን ሰው ዓለማመንና የኃጢአተኞችን ሃይማኖት የለሽነት ይፈቅዳል። ያለዚህ ፈቃድ አለማመንም ሆነ

በመጽሐፍ ቅዱስ መሠረት፥ ጽድቅ የሰው ባሕሪይ ሳይሆን የተሰጠ ነገር ነው:-

«መጽሐፍስ ምን አለ? አብርሃምም እግዚአብሔርን አመነ፤ ጽድቅም ሆኖ ተቆጠረለት። ለሚሠራ ደመወዝ እንደ ዕዳ ነው እንጂ እንደ ጸጋ አይቆጠርለትም፤ ነገር ግን ለማይሠራ ኃጢአተኛውንም በሚያጸድቅ በሚያምን ሰው እምነቱ ጽድቅ ሆኖ ይቆጠርለታል» (ሮሜ 4:3-5 በተጨማሪ ያዕ. 2:23 ተመልከት)።

«እግዚአብሔር በክርስቶስ ሆኖ ዓለሙን ከራሱ ጋር ያስታርቅ ነበርና በደላቸውንም አይቆጥርባቸውም ነበርና ...» (2ኛ ቆሮ. 5:19)።

በቁርዓን መሠረት ግን አላህ ከፈቀደ ኃጢአትም የሚሰጥ ነገር ነው። ሰው በአላህ ተገድዶ ኃጢአት የሚሠራ ከሆነ፥ ሊነቀፍ ይገባዋልን? (በተጨማሪ «እስልምና ስለ ራሱ ያለው አመለካከትና፥ ሌሎች ያላቸው አመለካከትና ምንነቱ» ገጽ 93-103 ተመልከት)!

## እስልምና ስለ ኃጢአት ያለው አገላለጽ

«... ተግባራትን ማክበር ጨዋነት ይባላል፤ እንዲሁም ችላ ማለት ወይም መጣስ ደግሞ ኃጢአት ይባላል። ችሮታና ኃጢአት ሕጋዊና ሕጋዊ ካልሆኑ ነገሮች የሚመጡ ናቸው።»

«በሁሉም ድርጊት ላይ ችሮታና ኃጢአት ይኖራሉ»። «ማናቸውንም የግድ መፈጸም ያለባቸውን መሠረታዊ ተግባራት አለመፈጸም ታላቅ ኃጢአት ይባላል። ሌሎች መፈጸም ያለባቸው ጥቃቅን ተግባራት አለመፈጸም ትንሽ ኃጢአት ይባላል። ቅዱሱ ነቢይ ያለምንም ማቋረጥ ሁልጊዜ ያደርጋቸው የነበሩትን ተግባራት አለመፈጸም ታላቅ ኃጢአት ነው። ትንሽ ኃጢአትን ያለማቋረጥ እየደጋገምን ስንሠራ ትልቅ ኃጢአት ይሆናል» (ሚሽካት 3 ገጽ 121-129)።

1. ቃፊርነት (አለማመን፥ መንፈሳዊ ክሕደት)
2. በማያቋርጥ ሁኔታ ‹ትንንሽ› ኃጢአቶች መሥራት

3. አላህ ምሕረት አያደርግልኝም ብሎ ተስፋ መቁረጥ
4. ከአላህ ቁጣ ለመዳን ታስቦበት የሚደረግ መከላከል
5. ሐሰተኛ ምስክር
6. አንድን ሙስሊም በውሸት በአመንዝራነት መክሰስ
7. እውነትን ለመናገር ምሎ ውሸት መናገር
8. የጥንቆላ ተግባር
9. የአልኮል መጠጦችን መጠጣት
10. ወላጅ የሌላቸውን ልጆች ንብረት መውሰድ
11. አራጣ ማበደር
12. ማመንዘር
13. ያልተለመደ ልዩ ወንጀል
14. ስርቆት
15. መግደል
16. ከከሐዲ ጠላቶች ጋር ከሚደረግ ውጊያ መሸሽ
17. ወላጆችን አለመታዘዝ

(ከ «የእስልምና መዝገበ ቃላት» ገጽ 594 የተወሰደ)።

የተለያዩ የኃጢአት ደረጃዎችን ለመለየት ብዙ ቃላቶችን ተጠቅመዋል:-

ከሐጢ-አ ለመሰናከል፥ ዓላማን መሳት፥ ስሕተት መሥራት፥ ሆን ተብሎ የተሠራ ኃጢአት (ሱረቱ 17፡31ን ተመልከት)።

(ከሀት ተመሳሳይ ሥርወ ቃሉ ነው)።

‹ዛንብ› ለ ኃጢአት፥ ጥፋት (ሱረቱ 24፡14ና 81፡9ን አወዳድር)።

‹ኢትም› ለ በሕግ የተከለከለ ማንኛውም ነገር፥ ትልቅ ኃጢአት

‹ሺርክ›/ሺርካ ለ ለአላህ እኩያ መጨመር፥ ብዙ አማልክት ማምለክ። (ከ «የእስልምና ኢንሳይክሎፒዲያ» ገጽ 250 የተወሰደ)።

‹ቀላል ኃጢአቶችን› በመልካም ሥራ ማካካስ ይቻላል፤ ‹ከባድ ኃጢአቶችን› ግን ‹ኤስቲግሐፋር› ይፈልጋሉ። ይህም ማለት:- ከአላህ ይቅርታ መፈልግ ነው።

በተጨማሪም ከኃጢአት ሁሉ ከባድ የሆነው «ለአላህ ሺርካ ማበጀት»፥ ‹ታውባህ› ወይም ንስሐ ያስፈልገዋል።



ቁርዓን እንዲህ ይላል:-

ሱረቱ 39፡53. በላቸው:- እናንተ በነፍሶቻችሁ ላይ ድንበር ያለፋችሁ ባሮቼ ሆይ! ከአላህ እዝነት ተስፋ አትቁረጡ፤ አላህ ኃጢአቶችን በመላ ይምራልና እነሆ እርሱ መሐሪው አዛኙ ነውና። (ድሐንብ)

እርግጥ ይህ ሐሳብ ከሌሎች ጋር ይቃረናል:-

ሱረቱ 3፡129. በሰማያት ያለው በምድርም ያለው ሁሉ የአላህ ነው፤ ለሚሻው ሰው ይምራል፤ የሚሻውንም ሰው ይቀጣል፤ አላህም መሐሪ አዛኝ ነው።

ሱረቱ 2፡284. በሰማያት ውስጥና በምድርም ውስጥ ያለው ሁሉ የአላህ ነው። በነፍሳችሁ ውስጥ ያለውን ብትገልጹ ወይም ብትደብቁ አላህ በርሱ ይቆጣጠራችኋል፤ ለሚሻውም ሰው ይምራል፤ የሚሻውንም ሰው ይቀጣል፤ አላህም በነገሩ ሁሉ ላይ ቻይ ነው።

<u>ቁርዓን ስለ ኃጢአት የሚያስተምረው ምንድነው?</u>

ሱረቱ 53፡32. (እነርሱ) እነዚያ የኃጢአትን ታላላቆችና አስጠያፊዎቹን የሚርቁ ናቸው፤ ግን ትናንሾቹ የሚማሩ ናቸው ጌታህ ምሕረተ ሰፊ ነውና። (ኢትም)

ሱረቱ 2፡81. አይደለም (ትነካችኋለች)፤ መጥፎን (ከሕደትን) የሠራ በርሱም ኃጢአቱ የከበበችው ሰው እነዚያ የእሳት ጓዶች ናቸው፤ እነርሱ

በውስጧ ዘውታሪዎች ናቸው።
ከሐጢ ’አ

ሱረቱ 17:31 ልጆቻችሁንም ድህነት በመፍራት
አትግደሉ፤ እኛ
እንመግባቸዋለን፤ እናንተም
(እንመግባለን)፤ እነሱን መግደል
ታላቅ ኃጢአት ነውና።
(ከሐጢ-አ)

ሱረቱ 4:48. አላህ በርሱ ማጋራትን በፍጹም
አይምርም፤ ከዚህ ሌላ ያለውንም
(ኃጢአት) ለሚሻው ሰው
ይኖራል። በአላህም የሚያጋራ
ሰው ታላቅ ኃጢአት በእርግጥ
ቀጠፈ። (ሺርክ/ሺርካ)

ሱረቱ 4:137. እነዚያ...ክሕደትንም የጨመሩ፥
አላህ ለነሱ የሚምራቸውና ቅኑን
መንገድ የሚመራቸው
አይደለም።

ሱረቱ 47:34. እነዚያ የካዱ (ሰዎችንም) ከአላህም
መንገድ ያገዱ፥ ከዚያም እነሱ
ከሀዲዎች ሆነው የሞቱ አላህ
ለነሱ በፍጹም አይምርም።

ሱረቱ 46:31. ወገኖቻችን ሆይ የአላህን ጥሪ
ተቀበሉ፤ በእርሱም እመኑ፤
(አላህ) ከኃጢአቶቻችሁ ለናንተ
ይኖራልና፤ ከአሳማሚ ቅጣትም
ያድናችኋልና። (ደሐንብ)

በአዲስ ኪዳንም ሆነ በብሉይ ኪዳን ያለውን የደኅንነት ትምህርት ስንመለከት፥ ከኃጢአት መሥዋዕት፥ የኃጢአት ተሸካሚ፥ ለኃጢአት ይቅርታ ከሚደረግ የደም መፍሰስ ለይተን ልናየው አንችልም። እስልምና ስለ እግዚአብሔር፥ ስለ ሰውና ስለ ኃጢአት በሚያቀርበው ትምህርት፥ እግዚአብሔር ለኃጢአት ይቅርታና ለደኅንነት ከሰው ምን እንደሚፈልግ በበቂ ሁኔታ አይገልጽም።



ሱረቱ 53:31 እነዚያን ያጠፉትን በሠሩት ሊቀጣ፥
እነዚያን ያሳመሩትንም በመልካሚቱ
(ገነት) ሊመነዳ (ዋጋቸውን ሊከፍል)
(የጠመመውንና የቀናውን ያውቃል)።

32. (እነርሱ) እነዚያ የኃጢአትን
ታላላቆችና አስጠያፊዎቹን የሚርቁ
ናቸው፤ ግን ትናንሾቹ የሚማሩ
ናቸው። ጌታህ ምሕረተ ሰፊ ነውና።

ሱረቱ 33:70. እናንተ ያመናችሁ ሆይ! አላህን ፍሩ፤
ትክክለኛንም ንግግር ተናገሩ።

71. ሥራዎቻችሁን ለናንተ ያበጅላችኋልና
ኃጢአቶቻችሁንም ለናንተ
ይምርላችኋል፤ አላህንና
መልእክተኛውን የሚታዘዝም ሰው
በእርግጥ ታላቅን ዕድል አገኘ።

ሱረቱ 35:7. እነዚያ የካዱት ለነርሱ ብርቱ ቅጣት
አለባቸው፤ እነዚያም ያመኑትና በጎ
ሥራቸውን የሠሩት ለነርሱ
ምሕረትና ታላቅ ምንዳ አላቸው።

ሱረቱ 8:29. እናንተ ያመናችሁ ሆይ! አላህን ብትፈሩ
የእውነት መለያን ብርሃን
ያደርግላችኋል፤ ክፉ
ሥራዎቻችሁንም ከናንተ ላይ
ያብስላችኋል፤ ለእናንተም
ይምራችኋል፤ አላህም የታላቅ
ችሮታ ባለቤት ነው።

ሱረቱ 4:16. እነዚያም ከናንተ ውስጥ (ዝሙትን)
የሚሠሩትን አሰቃዩአቸው፤
ቢጸጸቱና ሥራቸውንም ሊያሳምሩ
ከነርሱ ተገቱ (አታሰቃዩአቸው)፤
አላህ በነርሱ ላይ ጸጸትን ይቀበላል።
አላህም አዋቂ ጥበበኛ ነው።

ሱረቱ 25፡71. ተጸጽቶ የተመለሰም ሰው መልካምን
የሠራ እርሱ የተወደደን መመለስ
ወደ አላህ ይመለሳል።

ሱረቱ 14፡10. መልእክተኞቻቸው፡-
ሀከኃጢአቶቻችሁ እንዲምራችሁ
ወደተወሰነ ጊዜም (ያለቅጣት)
እንዲያቆያችሁ የሚጠራችሁ
ሲሆን፥ ሰማያትንና ምድርን ፈጣሪ
በሆነው አላህ (በመኖሩ) ጥርጣሬ
አለን?ሀ አሏቸው።

ሱረቱ 8፡38. ለነዚያ ለካዱት በሏቸው፡- ቢከለክሉ
ለነሱ በእርግጥ ያለፈውን (ሥራ)
ምሕረት ይደረግላቸዋል።

## ሐዲስ ስለ ኃጢአት ምን ያስተምራል?

«አብዱላህ-ቢ-ማስውድ እንደዘገበው፡- አንድ ሰው መሐመድን እንዲህ ብሎ ጠየቀው፡- ... በአላህ ፊት በጣም ትልቁ ኃጢአት ምንድነው? እሱም ሲመልስ፡- ለአላህ እኩያ ወይም ሽርክ ስታበጅለት ነው።...ከዚህስ ቀጥሎ? እሱም ሲመልስ፡-ልጅህን መግደል ነው። ከዚህስ ቀጥሎ? እሱም ሲመልስ ... ማመንዘር ...»

«አብዱላህ-ቢ-ዓኢሚር በዘገበው መሠረት፡- የአላህ መልእክተኛ እንዲህ ብሏል፡- በጣም ታላላቆቹ ኃጢአቶች፡- ለአላህ እኩያ ማድረግ፥ ወላጆችን ዓለመታዘዝ፥ ነፍስ መግደልና በሐሰት መማል ናቸው»።

«አቡ ሁራይራህ እንደዘገበው፡- የአላህ መልእክተኛ እንዲህ ብሏል፡- ሰባቱን ጎጂ ነገሮች አስወግዱ ... ለአላህ እኩያ ማበጃት፥ ጥንቆላ፥ አላህ እንደደነገገው በሕጋዊ መንገድ ብቻ ካልሆነ በስተቀር ነፍስ መግደል፥ ወላጅ የሌላቸውን ልጆች ንብረት ለራስ መውሰድ፥ በቅዱስ ጦርነት ጊዜ ወደኋላ ማፈግፈግ፥ ቁምነገር የሌላቸውንም ሴቶች ማመን»።

«አቡ ሁራይራህ በተጨማሪም እንደዘገበው፡- የአላህ መልእክተኛ እንዲህ ብሏል፡- በእውነት አላህ ተከታዮቹ እስካላደረጉት እስካልሞከሩት ድረስ ደረቶቻቸው ወደ ክፉት መፍጠናቸውን ይቅር ይላል»።



«ሙአዝ እንዲህ ብሎ ዘግቧል፡- የአላህ መልእክተኛ መመሪያ የሚሆኑኝ አሥር ምክሮች ሰጥቶኛል ከእነዚህም መሐል፡- ከአላህ ጋር ምንም ነገር አታወዳድር ... ወላጆችህንም የማትታዘዝ አትሁን ... መጸለይ ያለባቸውንም ጸሎቶች አታቋርጥ ... የወይን ጠጅ አትጠጣ ... ከቅዱስ ጦርነት ላለመሸሽ ተጠንቀቅ ... እንዲሁም በራስህ መንገድ ለቤተሰብህ ድጎማ አድርግ የሚሉ ናቸው።»

«ሳፍዋን-ቢ-አሳይ እንዲህ ብሎ ዘግቧል ... ከአላህም ጋር ምንም አታወዳድር፤ አትስረቅ፤ አታመንዝር፤ ነፍስ አትግደል፤ የዋህ የሆነውን ሰው ለማስገደል ወደ ባለሥልጣን አትውሰድ፤ ጥንቆላን አትለማመድ፤ ወለድ አትውሰድ፤ ንጹሕ የሆነችን ሴት አትሳደብ፤ ከጦርነትም ወደ ኋላ አትመለስ ...»።

መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ዓይነቱን የኃጢአት አመለካከት በሙሉ እንደሚቃረን እናውቃለን። በኃጢአት ላይ ያለለዘብተኛ አመለካከትና በገፍ የሚሰጥ ምሕረትንና ይቅርታን መጠበቅ ከታከለበት፥ አዳኝ የሆነውን ጌታ አስፈላጊነት ያስወግዱታል። እስልምና ውስጥ መግባትና ሕግጋቱንም መጠበቅ በቂ ሆነው ይቆጠራሉ። እኛ ክርስቲያኖች ይህንን መቀበል ያስቸግረናል። (ከላይ የተጠቀሱት ጥቅሶች ከሚሻካቱል ማሳቢህ 3 ገጽ 129-139 የተወሰዱ ናቸው)።

## ንስሐ፥ ይቅርታ፥ የኃጢአት ስርየት

ታማኝ የሆኑ ሙስሊሞች የሚኖሩትም ሆነ የሚያደርጉት ሁሉ በታላቅ አክብሮትና ፍርሃት መሆኑን እናውቃለን። በመቃብርም ሆነ በገሃነም ካለው ቅጣት ለማምለጥ ሲሉ ሕጎቹን በሙሉ ለመጠበቅ ራሳቸውን ያስገድዳሉ። እውነተኛ ሙስሊሞች የሞትን ቀንና የፍርድን ቀን እጅግ ይፈራሉ። ፍርሃት ደግሞ በእያንዳንዱ ቀን የምናደርገውን ነገር ይወስናል፤ ይህም ሆኖ ሳለ ማንኛውም ሙስሊም የኃጢአት ይቅርታ ማግኘቱንና በእግዚአብሔር ፊት የዘላለም ሕይወት እንዳለው እርግጠኛ መሆን አይችልም።

ሱረቱ 7፡8. ትክክለኛውም ሚዛን የዚያን ቀን
ነው፤ ሚዛኖቻቸው የከበዱላቸው
ሰዎችም እነዚያ እነርሱ
የፈለጉትን ያገኙ ናቸው።
9. ሚዛኖቻቸው የቀለሉባቸው ሰዎችም እነዚያ
እነርሱ ተአምራቶቻችንን ይክዱ በነበሩት
ምክንያት ነፍሶቻቸውን ያከሰሩ ናቸው።

ነገር ግን እነዚህ ጥቅሶች በሙሉ ቀጥሎ ከተጠቀሱት ጋር ይቃረናሉ፡-

ሱረቱ 76፡29. ይህቺ መገሠጫ ናት፡ ያሻም
ሰው ወደ ጌታው መንገድን
ይይዛል።

30. አላህም ካልሻ በስተቀር አትሹም፤
አላህ አዋቂ ጥበበኛ ነውና።

ሱረቱ 32፡13. ባሻንም ኖሮ ነፍስን ሁሉ
ቅንነቷን (እምነቷን) በሰጠናት
ነበር፤ ግን ገሃነም፥
ከአጋንንትና ከሰዎች
የተሰበሰቡ ሆነው በእርግጥ
እመላለሁ ማለት ቃሉ ከኔ
ተረጋግጧል።

ሱረቱ 16፡93. አላህም ቢሻ ኖሮ አንዲት ሕዝብ
ባደረጋችሁ ነበረ፤ ግን
የሚሻውን ሰው ያጠምማል፤
የሚሻውንም ሰው ያቀናል፤
ትሠሩት ከነበራችሁትም ሁሉ
በእርግጥ ትጠየቃላችሁ።

ሱረቱ 7፡178. አላህ የሚያቀናው ሰው ቅን
እርሱ ነው፤ የማያጣመውም
ሰው እነዚያ ከሳሪዎቹ እነሱ
ናቸው።

179 ከአጋንንትም ከሰዎችም ብዙዎችን
ለገሃነም በእርግጥ ፈጠርን፤

## ማጠቃለያ

ከዚህ ሁሉ እንደምንመለከተው በእስልምና ይቅርታ የሚገኘው ያለ ስርየትና ያለመታረቅ እንዲሁም ያለ ደም መሥዋዕት ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ መስፈርቶች መሠረት እስልምና ደኅንነት አያስገኝም። እንዲያውም የባሰ ሰዎችን እግዚአብሔር (መጽሐፍ ቅዱስ) ከሚጠይቃቸው መሠረታዊ ነገሮች ላይ እንዳያምኑ ያደርጋቸዋል። እግዚአብሔር «ደም ሳይፈስ ስርየት የለም» እንዲሁም የልጁ የኢየሱስ ደም ብቻ



ከኃጢአት ሁሉ እንደሚያነፃን ተናግሯል (ዕብ. 9፡22 እና 1 ዮሐ. 1፡7)። እስልምና በዚህ ሁሉ እግዚአብሔር ያለውን ሙሉ በሙሉ ይቃረናል! በዚህ መሠረት እስልምና «ልዩ ወንጌል» ነው! (ገላ 1፡6-9)። (በግሪክ ለ ሔትሮስ ኢቫንጊሊዮን ለ ልዩ የሆነ የሌላ ነገር)።